
# ትንሣኤ



በጎማ ወረዳ የሬሜቤ ቅዱስ ሚካኤል ካህናት በልማት ሥራ ላይ



የለገዳዲ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በክፍ ሀ/ ስብከት በሊሙ አውራጃ

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ፤ሥርዓትና ዜና፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጕሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»


አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፤
ም/ ከንፈ ርግብ ማርቆስ




በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ፤


# ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**


ደብዳቤዎች ........ ፩
በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ አንዋደድ ........ ፪
የክርስቶስ ትንሣኤ የአማንያን ሁሉ ተስፋ ነው ........ ፬
በዓለ ዕርገት ........ ፮
ዜና ሊቃውንት ........ ፯
የግንቦት ልደታ ንፍሮ ከምን መጣ? ........ ፰
መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት (ነፋስ) ........ ፲
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........ ፲፪
የቤተሰብእ ዓምድ ........ ፲፫
በዓለ ሃምሳ ........ ፲፬
አጭቃን ኪዳነ ምሕረት ወደ ጥንት ደብርነቷ ተመለሰች ........ ፲፮
የጤና ዓምድ (የተቅማጥ በሽታ) ........ ፲፰
የግብርና በረከት ........ ፳
የጻድቁ አቡነ ዮሴፍ ታሪክ ........ ፳፩
ማርያም መግደላዊት ........ ፳፫
በዝግ ቤት ታያቸው ........ ፳፬


ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ፤
አዲስ አበባ ፡-

ከሁሉም አስቀድሜ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መንፈሳዊ ሰላምታዬን እየገለጽኩ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች አቀርባለሁ ።

፩ኛ/ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ መምህር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓርብ የስቅለት ዕለት ማታ ነፍሳትን ከሲኦል አውጥቶ ወደ ገነት አስገብቷቸዋል ። ብለው አስተማሩን ።

በሌላ ጊዜ ደግሞ አንዱን አስተማሪ ማዕዶት ማለት ምን ማለት ነው ብዬ ብጠይቃቸው የቃሉ ትርጉም ማዕዶት ማለት መሸጋገሪያ ማለት ነው በትንሣኤ ማግስት በሚከበረው ማዕዶት በሚባለው ዕለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የስቅለት ዕለት ዓርብ ማታ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ነፍሳትን አውጥቶ የማዕዶት ዕለት ወደገነት ያስገባበት (ያሸጋገረበት) ቀን ነው ሲሉ አስረዱኝ ስለዚህ የሁለቱም መምህራን ቃል የተለያየ በመሆኑ እሳቡ በልቡናየ ውስጥ ይወጣል ይወርዳልና እናንተ በትንሣኤ መጽሔት አብራሩልኝ እባካችሁ ።

፪ኛ/ በትንሣኤ ሰሞን አዳም ሐሙስ የሚባል ዕለት አለአዳም ሐሙስ የተባለበትን ምክንያት እንድታስረዱኝ ስል በትህትና እጠይቃለሁ ።

ወጣት ሞገስ ካሣዬ
ከአላማጣ የሰንበት ት/ቤቶች ተማሮች

<u>መልስ</u> ፡

ሞገስ ካሣዬ ስለአቀረብክልን መንፈሳዊ ሰላምታ እናመሰግናለን ለጠየቅሃቸውም ጥያቄዎች መልሶቻቸውን እንደሚከተለው እናቀርባለን ። ከመጀመሪያው ጥያቄህ ላይ የሁለት መምህራን ትምህርት የተለያየ መስሎ ስለታየህ ለዚያ ማብራሪያ እንዲሰጥህ ጠይቀሃል ይኸውም አንደኛው መምህር ነፍሳት ከሲኦል የወጡትና ወደገነትም የገቡት በዕለተ ስቅለት ዓርብ በሠርክ ነው ። ሲሉ ሌላው መምህር ደግሞ የትንሣኤ ማግሥት የማዕዶት ዕለት ነፍሳት ወደገነት እንደገቡ አድርገው በማስተማራቸው ነው ።

የመጀመሪያው አስተማሪ ያስተማሩት ትምህርት ትክክል ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓርብ በስድስት ሰዓት ተሰቅሎ በመስቀል ላይ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ከቆየ በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው በገዛ ፈቃዱ ለይቷል ወዲያውም በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ በሲኦል የነበሩትን ነፍሳት አውጥቶ ወደገነት ሲያስገባ ሥጋው ወደ መቃብር ወርዷል ይህንም ሐዋርያው ጴጥሮስ "በሥጋ ሞተ በነፍስ ግን ሕያው ሆነ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወህኒ ቤት ለነበሩት ነፍሳት ነፃነትን ሰበከላቸው" በማለት ገልጾታል ። ፩ኛ ጴጥ. ፫. ፲፰ ።

ነገር ግን ሁለተኛው አስተማሪ በትንሣኤ ማግሥት ነው ነፍሳትን ወደገነት ያስገባቸው ብለው ማስተማራቸው ነፍሳት ከሲኦል የወጡበት ቀን መታሰቢያ የሚከበርበትን ዕለት መሠረት በማድረግ ይሆናል እንጂ ነፍሳት በዕለተ ዓርብ ከሲኦል አልወጡም ወደገነትም አልገቡም ማለታቸው አይደለም ለጠየቁ የምንሰጠው መልስ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስረዱን ነፍሳት ከሲኦል ወጥተው ወደገነት የገቡት በዕለተ ዓርብ በሠርክ መሆኑን ነው ።

ሁለተኛው ጥያቄ በትንሣኤ ሰሞን አዳም ሐሙስ እየተባለ ስለሚጠራው ዕለት ነው ። አዳም ሐሙስ እየተባለ የሚጠራው ዕለት የሁላችን አባት አዳም አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሙሉ በመንጸፈ ደይን ወድቆ በእግረ አጋንንት ተጠቅጥቆ ከኖረ በኋላ ክርስቶስ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ተሰቅዬ ሞቼ አድንኃለሁ ባለው መሠረት መጥቶ የተናገረውን ቃል ስለፈጸመለት ያንን ለማስታወስ አዳም ሐሙስ እየተባለ በየዓመቱ በትንሣኤ ሰሞን ይከበራል ።

## በዝግ ቤት .......


ወደገጽ ፲፱ ዞሯል


<u>ካከላቸው በመቆም ተገልጾ ሰላም ለእናንተ ይሁን በማለት የተወጋውን ጎኑን የተቸነከረ ዕጅ ዕግሩን አሳያቸው በመካከላቸው ተገልጾ ከታያቸው በኋላ እንጀራውን አንስቶ በመቁረስ</u> ለእነሱም ሰጣቸውና እርሱም በፊታቸው በላ መንፈስ ያዩ መስሎአቸው ስለ ደነገጡ ለመንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና የእኔን አጥንቴንና ሥጋዬን ዕዩት ብሎ አሳያቸው ።

ቶማስ በዚህ ጊዜ ስለ አልነበረ እንደገና በስምንተኛው ቀን አሁንም በዝግ ቤት እንደተቀመጡ በመካከላቸው በመገኘት ከታየ በኋላ ቶማስ ጣትህን አንጣና የተወጋውን የተቸነከረውን ዕጅን ዕግሬን እይ ብሎ አሳየውና አይቶ አመነ ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ አስቀድሞ የተገለጸላት ለማርያም መግ


ተከታዩ ወደ ገጽ ፫ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ አንዋደድ

፩ኛ ዮሐ ፫. ፲፰

የሚበላው አጥቶ የተራበ ፤ የሚጠጣው አጥቶ የተጠማ ፤ የሚለብሰው አጥቶ የተራቆተ ፤ የሚጠጋበትና የሚጠለልበት አጥቶ የቀን ሐሩር የሌሊት ቁር የሚፈራረቅበትን ችግረኛ በተመለከተን ጊዜ ሁላችንም እናዝናለን ፤ እንተክዛለን ከንፈራችንም እንመጣለን ፤ እንገታችንም እናዘነብላለን ፤ አንዳንዶቻችን ከዚህ አልፈን ተርፈን ደረታችን እንደቃለን እንባችንም ከማፍሰስ እንደርሳለን ።

አጥቶ የተራበው የተጠማው የተራቆተው ችግረኛ የሥጋችን ቁራጭ ፤ የአጥንታችን ፍላጭ ነውና ልናዝንለትና ልናለቅስለት ይገባናል ፤ ይሁን እንጂ የተቸገረውን ወገናችን ከችግሩ ልናላቅቀው የምንችለው በልቅሶ ብቻ አይደለም ። ገንዘባችን ዕውቀታችንና ጉልበታችን አስተባብረን ከችግሩ ረግረግ የሚወጣበትን ቀና መንገድ ስንቀይስለት ነው ።

ይህንንም እንግዚአብሔር አምላካችን ሠርቶ ባሳየን ተግባር ለመረዳት እንችላለን የመጀመሪያው ሰው አዳም የፈጣሪውን ትእዛዝ በማፍረሱ ከባድ ችግር ደረሰበትና እጅግ በጣም ተጨንቀ ወደፈጣሪውም ጮሖ አለቀሰ ፈጣሪውም ችግሩን ተመልክቶ ጩኸቱን ሰምቶ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ተሰቅሎ ሞቶ ተነሥቶ ከደረሰበት ችግር ሁሉ ነፃ እንደሚያወጣው ነገረው ፤ በቃል ብቻ ነግሮት አልቀረም በሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት ከድንግል ማርያም ተወልዶ ከኃጢአት በስተቀር ችግሩን ሁሉ እንደሰዎች በመካፈል ፴፫ ዓመታት ከ፫ ወራት ከቆየ በኋላ ከፍዳው ነፃ አድርጐታል ።

እንዲሁም ማርታና ማርያም ወንድማቸው አልዓዛር በሞተባቸው ጊዜ በጣም ኃዘን ተሰማቸው በዚያ ዘመን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ተገልጾ ሙት ያስነሣና ድውይ ይፈውስ ስለነበር ወደ እርሱ ሄደው የወንድማቸውን የአልዓዛርን መሞት ነገሩት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አልዓዛርን ከሞት ማዳን የማይሳነው ከሃሊ አምላክ ቢሆንም የሰው ልጆችን ወዳጅና የኃዘናቸውና የችግራቸው ተካፋይነቱን ለማስረዳት አልቅሷል ግን በልቅሶ ብቻ ተወስኖ አልቀረም ወዲያው አልዓዛር ወደተቀበረበት መቃብር ሂዶ አልዓዛር አልዓዛር ብሎ በመጥራት ከመቃብር አሥነሥቶ በሕይወተ ሥጋ እንዲኖር አድርጐታል ።

ይህ ሁሉ የሚያስረዳን የተቸገሩትን ወገኖቻችን የችግራቸው ተካፋዮች መሆን የሚገባን በቃል ብቻ ሳይሆን በሥራም ጭምር መሆኑን ነው ። ሐዋርያው ያዕቆብ ወንድም ወይም እህት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብም ቢያጡ ከእናንተ አንዱም በደኅና ሂዱ እሳትም ሙቁ ከብርድ ትድናላችሁ ምግብንም ተመገቡ ትጠግባላችሁ ቢላቸው ለሰውነት የሚያስፈልጉትን ካልሰጣቸው ምን ይጠቅማቸዋል ። እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው ። ሲል ተናግሯል ። ያዕቆብ ፪. ፲፭ ።

ሐዋርያው ዮሐንስም በዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው ሰው ወንድሙ አጥቶ ሲቸገር አይቶ ያልራራለት ማንም ቢኖር የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል ? ልጆች ሆይ ! በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ አንዋደድ ይላል ፩ኛ ዮሐ ፫. ፲፭ ።

አባቶቻችንም በምሳሌ ሲናገሩ "የቃል ዘመድ ከገበያም አይገድ" ይላሉ ፤ ለችግረኛ ወገን ማዘንና መራራት ዋጋ ከእግዚአብሔር ሊያሰጥ የሚችለው ቃል ብቻ ሳይሆን ሥራም ሲጨመርበት ስለሆነ በሀሳባችንም በሥራችንም በገንዘባችንም የተቸገሩትን ወገኖቻችን ልንረዳቸው ይገባናል ።

አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ለፍርድ ቀረበና አምላኬ ሆይ ወደእኔ ተመልከት ሕግህን ጠብቄያለሁ ሐሠትን አልተናገርኩም ጭካኔንትን አልፈጸምኩም ንጽሕናን አላጐደልኩም ጌታ ሆይ እጆቼም ንጹሐን ናቸው አለ ። እግዚአብሔርም በሚወደው ሰው ላይ አድሮ እውነት ነው እጆችህ ንጹሐን ናቸው ዳሩ ግን ባዶዎች ናቸው ሲል መለሰለት ይባላል ። ሐዋርያት መንግሥተ ሰማያት መቼ ትመጣለች ብለው ጌታችን ቢጠይቁት መንግሥተ ሰማያት በመካከላችሁ ናት ሲል አስረድቷቸዋል ። ሉቃስ ምዕ. ፲፯ ቁጥር ፳ መንግሥተ ሰማያት በመካከላችሁ ናት ማለትም ከወገኖቻችን መካከል የተራቡትን በማብላት የተራቆቱትን በማልበስ የተቸገሩትን በመርዳት የምትገኝ ናት እንጂ በሌላ መንገድ ለመገኘት አትችልም ማለት ነው ።

አንድ ሊቅ "ገንዘብን አውጥቶ በማደል የድሆችን ችግር ለማስወገድ አይቻልም ድሆች በሽተኞችና ጕስቋሎች እንደሌሎች ለመኖር መብት እንዳላቸው ያውቃሉን ይልና አሳቡን በመቀጠል ለእነርሱ ማድረግ የሚገባን ከገንዘባችን መስጠት ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቦቻቸውና ለራሳቸው ሠርተው እንዲያገኙ ማድረግ ነው ችግረኞችን ማፍቀር ማለትም ከሥቃያቸውና ከኃዘናቸው ከተስፋቸውና ከደስታቸው ስንካፈልና የእኛንም ስናካፍላቸው ነው ብሏል ።

ኒውተን የተባለው ሊቅም "ሰዎችን መለያያግንቦችን በብዛት ሠራን መገናኛ ድልድዮችን ግን በብዛት አልሠራንም በማለት ተናግሯል ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኘን ዋናው ድልድይ ለችግረኞች ወገኖቻችን የምናሳየው የርኅራኄ ተግባር ነው ።

ሐዋርያው ዮሐንስ እንደተናገረው የምናያቸውን ወገኖቻችን እየጠላን የ ማናየውን እግዚአብሔርን እንወዳለን እያልን ብንናገር ሐሠተኞች እንጂ እውነተኞች አንባልም ።

በሀገራችን በደረሰው ድርቅ ምክንያት ብዙዎች ወገኖቻችን በችግር ላይ መገኘታቸውን ሁላችንም እናውቃለን ። ለእነዚህ ችግረኞች ወገኖቻችን ሁሉም በተቻለው መጠን የስጦታ እጁን በመዘርጋት ላይ ይገኛል ። ችግረኞችም ለጊዜው የረኃብና የብርድ መከላከያ የሚሆናቸው ርዳታ በማግኘታቸው ጊዜያዊ ደስታ ሊሰማቸው ይችላል ።

ከላይ እንደተገለጸው ለችግረኞች ማድረግ የሚገባን ከገንዘባችን መስጠት ብቻ ሳይሆን ራሳቸው ሠርተው እንዲያገኙ ማድረግ መሆኑ አያጠራጥርም አሁን መንግሥት በረኃብ ቀጠና የተያዙትንወገኖቻችን ሠርተው ወደሚያገኙበት ስፍራ በማዛወር ላይ ይገኛል እንደዚህ ያለው ተግባር የተቀደሰ በመሆኑ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም የገንዘብና የቁሳቁስ ርዳታ ከማድረጓም ሌላ ለሰፈራ ጣቢያዎች ድንኳኖችን በመስጠትና ሠራተኞቿንም በመመደብ አገልግሎት ከመስጠቷም ጋር ካህናትም ችግረኞች ወገኖቻችን በትምህርተ ወንጌል እንዲያጽናኑ ማድረጓ የተረጋገጠ ነው ።

ሐዋርያው በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ አንዋደድ ያለው ቃል አሁን በሥራ በመተርጐም ላይ ይገኛል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊትነቷ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ጭምር ስለሆነ ምእመናንን ሁሉ ደስ የምታሰኝና የምታስመካ ናት በእውነት እንጂ በቃልና በአንደት ብቻ አንዋደድ ማለትም እንደዚህ ሐዋርያዊነት በተግባር ሲገለጽ ነው ።

## በዝግ ቤት .......

ከገጽ ፩ የዞረ

ደላዊት መሆኑ ተገልጿል፡- ከዚያም በኋላ ደቀ መዛሙርቱ በዝግ ቤት ተሰብስበው ስለሕማሙ ስለሞቱና ስለትንሣኤው ሲወያዩ በመካከላቸው በመገኘት ሰላም ለሁላችኑ ይሁን የሚለውን ቃል አሰምቶ ምትሐት ነው በማለት እንዳይጠራጠሩ የተቸነከሩ እጆቹንና እግሮቹን የተወጋውን ጐኑን ማሳየቱ ተጠቅሷል ።

ይህም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ስም አምነው ስለሕማሙ ስለሞቱ ከሚመሰክሩና ከሚያስተምሩ ምእመናን ጐን የማይለይ መሆኑን ያስረዳናል ሰላም የሚለውን የሕይወት ቃል እንዲያሰማን ሁላችንም ስለ እርሱ ሕማምና መከራ ሞትና ትንሣኤ መመስከርና ማስተማር ይገባናል ።

ቀ. ገብረ መስቀል ቸኮል





www.ethiopianorthodox.org

# የክርስቶስ ትንሣኤ የአማንያን ሁሉ ተስፋ ነው

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቶ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብርም አድሮ ተነሣ መሰቀሉን መሞቱንና እንዲሁም መነሣቱን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመረዳት ይቻላል ። ከዚህ ላይ ጌታ ክርስቶስ የተሰቀለው ? ለማን ነው ? የተነሣውስ ለማን ነበር ። ክርስቶስ የተሰቀለውና የሞተው እንዲሁም የተነሣው ለአዳም ልጆች ነበር ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ ቀዳማይ አዳምን ለማዳን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ ።

ከመሞቱ በፊት ብዙ ፀዋትወ መከራን ተቀበለ የተለያዩ ፀዋትወ መከራ በለበሰው ሥጋ ላይ ተፈራርቀውበታል ግን የክርስቶስ መስቀል የእኛ ድህነት ሆነ የክርስቶስ ትንሣኤም በኩረ ትንሣኤያችን ነው ለሚያምኑት ሁሉ የክርስቶስ ትንሣኤ ትንሣኤ ዘለሕይወት ነው እንግዲህ ወዲህ ክርስቲያኖች (ሰዎች) መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስ የለባቸውም ክርስቶስ ዕዳ ደብዳቤአቸውን ከላያቸው አጥፍቷል ። በክርስቶስ ጥላ ሥር ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ትንሣኤ ዘለነፍስ አላቸው ስለዚህ ትንሣኤ ዘለክብር ያላቸው አማንያን ሁሉ በትንሣኤ ዘለሥጋ ውስጥ የተዋጡትን ወገኖች ጭምር መርዳት አስፈላጊ መሆኑን መዘንጋት የለባቸውም በክርስቶስ ሞት ሞትን አሸንፈናል በክርስቶስም ተነስተናል የክርስቶስም ትንሣኤ የእኛ ትንሣኤ ነውና ምክንያቱም ራሱ ክርስቶስ የሞተው ለእኛ ሲል ነው ። የተነሣውም ለእኛ ሲል ነው ። ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት ማለትም የምዕመናን ፍቅር እግዚአብሔር ወልድን ከሰማዊ ዙፋኑ አውርዶ እሞት ድረስ አደረሰው የተባለውን ኃይለ ቃል ብናስታውስ ክርስቶስ ምን ያህል ምዕመናንን እንደሚያፈቅርና በመጨረሻም ሕይወቱን አሳልፎ እንደ ሰጠ ነው ። ምዕመናን ከዚህ ላይ መማር የሚገባቸው ምንድር ነው ? ክርስቶስ ሕይወቱን ለምዕመናን አሳልፎ እንደ ሰጠው ሁሉ እንዲሁም ምዕመናን እቅማቸው በሚፈቅደው መጠን ለወገን ተፈላጊውን ዕርዳታ ሁሉ መከፈል ይኖርባቸዋል ። ይህ ሲሆን ነው የትንሣኤን ብርሃን ለማየት የሚቻለው ትንሣኤን የምናከብረው ለምንድር ነው? የምን አከብረውስ በምን ላይ የተመረኰዘ ነው ?

እርግጥ የምናከብረው ክርስቶስ ተነሣልን ብለን ነው ሊሆንም የሚገባ አክብሮት ነው የምናከብረውስ በምን ላይ የተመረኰዘ ነው ለሚለው ግን ልዩ ልዩ ምግብንና መጠጥን በማግበስበስ ሊሆን ይችላል እርግጥ ምግብ ከእራት አስፈላጊዎቹ ነገሮች (ነሰሲቲ) አንዱ ቢሆንም ቅሉ በመንፈስ ልንቃኝ የሚገባ ሌላ ዓቢይ ተግባር እንዲኖረን ያስፈልጋል ።

ይኸውም ለትንሣኤ የሚያበቃንን መንፈሳዊ ሥራ መሥራት እንዳለብን ነው ። ከክርስቶስ ጋር ለመነሣት ሕሊናችን አስቀድሞ ከክርስቶስ ጋር መታመም መስቀልና እንዲሁም መሞትም ይኖርበታል ። በዚህ አንፃርም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የማርታን ያህል እምነት እንዲኖራቸው በክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ይገደዳሉ ። ጌታ ክርስቶስ ወንድምሽ ይነሣል በአላት ጊዜ ማርታ ምስጢረ ትንሣኤን አስመልክታ በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ አለችው ኢየሱስም ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ። የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘለዓለም አይሞትም ይህን ታምኚያለሽን ? አላት እርሷም አዎን ጌታ ሆይ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ እኔ አምናለሁ አለችው ።

የዮሐንስ ወንጌል ም. ፲፩ ከቁ.፳፬ ላይ መመልከት ይቻላል። ማርታ ለኢየሱስ ከሰጠችው መልስና እንዲሁ ኢየሱስ ለማርታ ከአስረዳት ሕይወታዊ ቃል ለማወቅ እንደ ተቻለው በመጨረሻ ጊዜ የሰው ልጅ በትንሣኤ እንደሚነሣና ኢየሱስም ትንሣኤና ሕይወት እንደ ሆነ ለዚህ ሁሉ ግን እምነት አስፈላጊ መሆኑ ግልጽ ነው ። ኢየሱስ ለማርታ ሲያስረዳት በእርሱ የሚያምን ሁሉ ለጊዜው በአፀደ ሥጋ ከዚህ ዓለም ቢለይም ወይም ቢሞት በአፀደ ነፍስ ተመልሶ ሕያው እንደሚሆን ጥርጥር የሌለበት መሆኑን ጭምር ነበር በመጨረሻም ኢየሱስ ለማርታ የእምነት ፈተና አቀረበላት ማርታም ከኢየሱስ የቀረበውን የፈተና እምነት በመልካም ሁኔታ እንደ አለፈች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመረዳት ተችሏል ። የሚያምንብኝ ሁሉ ለዘላለም አይሞትም ይህን ታምኚየለሽን ? የሚል ነበር ። ከኢየሱስ ለቀረበው የእምነት ፈተና ማርታ የሰጠችው መልስ አዎን ጌታ ሆይ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ አውቃለሁ የሚል ነው ኢየሱስ ይህን ዓይነት መጠይቅ አሁን ለክርስቲያኖች እንደሚያቀርብ ጥርጥር አይኖርም መልሳቸው ግን ከማርታ መልስ እንዲርቅ አያሻም እርግጥ በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አትደነቁ ይላል ዮ. ፭ ከዚህ ላይ ሙታን ሁሉ እንደሚነሡና ከእነርሱ መልካም ሥራ የሠሩት ለሕይወት ትንሣኤ ክፉ ሥራ ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ እንደሚወጡ ያስረዳል ።

ከዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባ ቢኖር የክርስቶስ ትንሣኤ ለአማንያን ሁሉ ተስፋ ሲሆን ለኃጥአን ግን የፍርድ ትንሣኤ እንደሚሆንባቸው የተረጋገጠ ሐቅ ነው የሰዱቃውያንን ሥራ ለአንባብያን ግልጽ ለማድረግ ቢያስፈልግ በመሠረቱ ሰዱቃውያን በትንሣኤ ሙታን የማያምኑ የትንሣኤ ምስጢር የተሰወረባቸው ሕዝቦች ናቸው ። ለዚሁም አስረጅ ይሆን ዘንድ የሐዋርያውን ጳውሎስ አነጋገር ለመጥቀስ ይቻላል ። ጳውሎስ እኩሌቶቹ ሰዱቃውያን እኩሌቶቹም ፈሪሳውያን መሆናቸውን አይቶ ወንድሞች ሆይ እኔ ፈሪሳዊ የፈሪሳዊም ልጅ ነኝ ስለተስፋና ስለሙታን መነሣት ይፈረድብኛል ብሎ በሸንጎው ጮኸ ይህንም ባለ ጊዜ በፈሪሳውያንና በሰዱቃውያን መካከል ጥል ሆነ ሸንጎውም ተለየየ ሰዱቃውያን ትንሣኤም መልአክም መንፈስም የለም የሚሉ ናቸውና ፈሪሳውያን ግን ሁለቱንም ያምናሉ ። የሐዋርያት ሥራ ም. ፳፫ ከቁ ፮ ላይ መመልከት ይቻላል ።

ይህንን በመገንዘብ ከርዕሱ ላይ የክርስቶስ ትንሣኤ ለአማንያን ሁሉ ተስፋ ነው የተሰኘው ለአንባብያን ሁሉ ከሑት እንጂ ስውር እንደማይሆንባቸው በማመን ነው ጳውሎስ በትንሣኤና በመልአኩም መንፈስ በሚያምኑትና በማያምኑት መካከል ተገኝቶ የራሱ ድርሻ ግን በትንሣኤና በመልአክም በመንፈስ በሚያምኑት ክፍል መሆኑን የአረጋገጠበት ወቅት እንደነበረ በምንባቡ መሠረት ለመረዳት ይቻላል ።

ምክንያቱም ግልጽ ስለሆነ ነው የአማንያንም ተስፋ በትንሣኤና በመልአክም በመንፈስም ላይ የተመሠረተ (ያረፈ) ስለሆነ በኋለኛው ጊዜ ፍጹም ክርስቶስን መስለው እንደሚነሡ በምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ለሚያምን ሁሉ ኑፋቄ ልቡና እንደማይኖር የታወቀ ነው እርግጥ ይህ ምስጢር ትንሣኤ ሙታን ለሰዱቃውያን ግልጽ እንደማይሆን ከዚህ በላይ ከተዘረዘረው ምንባብ ለማወቅ ይቻላል በተ ጨማሪም ከማቴዎስ ወንጌል ም. ፳፪ ከቁ.፳፫ ላይ እንመልከት በዚያን ቀን ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ እርሱ ቀረቡ እንዲህም ብለው ጠየቁት መምህር ሆይ ሙሴ አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ቢሞት ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካ አለ ሰባት ወንድማማች በእኛ ዘንድ ነበሩ የፊተኛውም ሚስት አግብቶ ሞተ ዘርም ስለሌለው ሚስቱን ለወንድሙ ተወለት እንዲሁ ደግሞ ሁለተኛው ሦስተኛውም እስከ ሰባተኛው ድረስ ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ሞተች ሁሉ አግብተዋታልና በትንሣኤ ቀንስ ከሰባቱ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች ብለው ጠየቁት ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡም ስለ ትንሣኤ ሙታን ግን እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ ነኝ የሚል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም ።

ከዚህ ምንባብ ውስጥ ሁለት ኃይለ ቃሎች አሉት ሰዱቃውያን በትንሣኤ ቀን ከሰባቱ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች ብለው በጠየቁት ጊዜ ኢየሱስ በቀጥታ እንዲህ የሚል መልስ ሰጣቸው መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ የሚል አስደናቂና አምላካዊም መልስ እንደነበረ ከኃይለ ቃሉ ለመረዳት ይቻላል በዘመናቸው አንብበው ሊረዱ የሚገባቸው መጻሕፍት እንደነበሩ ግልጽ ነው እንዲሁም የእግዚአብሔር ኃይልም በዘመናት ሲሠራ እንደነበረም እሙን ነው ግን ማስተዋል ብቻ ስለተሳናቸው ከመሳሳት ደረሱ ከዚህም ሌላ አምላክ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ አምላክ ሕያዋን እንጂ አምላክ ሙታን ብቻ እንዳልሆነ ጭምር ታላቅ ትምህርት እንደሰጣቸው ለመገንዘብ የሚያዳግት አይሆንም ክርስቶስ ሙቶ እንደሚነሣ አስቀድሞ በነቢዩ ዳዊት ትንቢት የተነገረለት እንዲያውም ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመዘንቅሕ እምንዋም ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው እግዚአብሔር ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ተነሣ ተብሎ መተንበዩና በኋላም የትንሣኤው ምሥጢር ለእነግርያምና ግርያም መግደላዊት መገለጹ ለሚያምን ክርስቲያን የተደበቀ ምስጢር አይሆነውም ከዚህ ላይ ለምዕመናን በመልአኩ ላስገነዝባቸው የምወደው አቢይ ተግባር በእየዓመቱ የምናከብረው የትንሣኤ በዓል በአሁኑ ጊዜ ለየት ያለ መልክ አቅዋም እንዲኖረው አስፈላጊ መሆኑን ለመጠቆም ያህል ነው በድርቅ የተጐዱት ወገኖቻችን ጭምር በዓለ ትንሣኤን ለማክበር ፈቃደኞች ሆነው ሳሉ በችግር ምክንያቷ ተገቢ የቤት ቁሳቁስ እንደሚያጥርባቸው አሌ የማይባል ሐቅ ነው ። እነዚህ ወገኖቻችን በዓለ ትንሣኤን በተድላና በደስታ ለማክበር እንዲችሉ ከእኛ የሚጠበቀውን አስፈላጊ ዕርዳታ በቅድሚያ እንድንለግሣቸው በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ትንሣኤ ስም ቤተ ክርስቲያን ለምዕመናን ሁሉ መንፈሳዊ ጥሪ ታደርጋለች የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ትንሣኤ ለአማንያን ሁሉ የደስታ በዓል እንዲሆንላቸው በዚህ አጋጣሚ ቤተ ክርስቲያናችን ምኞቷን ትገልጻለች ።

ቄስ ኢያሱ ገብሬ





www.ethiopianorthodox.org

# በዓለ ዕርገት ፡

ዕርገት ማለት ምን ማለት ነው ። ወደ ታሪክ ማኅደርና ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ገባ ብለን ስንመለከት ዕርገትን አስመልክተው የሚነገሩ ቃላት በርከት ያሉ ናቸው ምሳሌም ቢ.የስራ ልግ ነቢዩ ኤልያስ በእሳት ሠረገላ እንዳረገ በ፪ኛ መጽሐፈ ነገሥት ም.፪ ፡ ቁ ፲፩ ላይ ተጽፎ ይገኛል ። እንደዚሁም ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና ይላል ። ዘፍጥ ፭ ፡ ፳፬ ።

ይህንን የመሰለ እርገት በተለያዩ መጻሕፍት እናነባለን ይህ በዓለ ዕርገት ብለን በርእሱ ላይ የጠቀስነውና መነሻ ያደረግነው ግን ከዚህ የተለየ ነው ። የነቢያት የጻድቃን ዕርገት ሳይሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያረገበት ዕለት ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ በምድራዊ ዓለም ፴፫ ዓመት ከ፫ ወር ከኖረ በኋላ ከሰማያዊ ዓለም ወደ ምድራዊ ዓለም የመጣው ሰውን ለማዳን ስለነበረ በአይሁድ ተንኮልና ምቀኝነት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ በ፫ኛው ቀንም መቃብር ክፈትልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል በሞቱ ሞትን አጥፍቶና ድል ነሥቶ ተነሣ ።

ከተነሣም በኋላ አንዳንድ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ እየተገለጠ ፵ ቀን ያህል በምድር ላይ ቆየ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ በ፵ ቀኑም ወደ ሰማይ ዐረገ ።

አዎ መጻሕፍተ ብሉያት ስለ እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መምጣት ሰው መሆኑንና ስለሰዎች ኃጢአትና በደልም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንደሚሞትና እንደሚነሣ ከተነሣም በኋላ ወደ ሰማይ እንደሚያርግ አስቀድሞ ትንቢት ሰፈሩ በሰፊው ተንትነው ገልጸውት ነበር ። በተለይም በየቀሀንቱና በገርነቱ ልበ አምላክ የሚል ዓቢይ ቅጽል የተቀጸለለት ነቢዩ ዳዊት ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት ቀደም ሲል በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ትንቢት ሲናገር (ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ ወእግዚእነ በቃለ ቅርን) ።

እግዚአብሔር በይባቤ በእልልታ ዐረገ ጌታችንም በክበሮና በመዝሙር ስለዚህ አምላካችን እናመስግን በማለት በሚገባ አስቀድሞ ተናግሯል ። ይህንን እግዚአብሔር አረገ ሲል ዳዊት ተናግሮት የነበረውንም ትንቢት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተግባር እንደፈጸመው እናያለን ።

ወንጌላዊ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ዕርገት አስታውሶ ሲጽፍ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ምስክሮች ትሆኑኛላችሁ ብሎ ከተናገረ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናም ከዐይናቸው ሠውራ ተቀበለችው" ብሏል ። የሐዋ.ሥ ፩፡፱ ወንጌላዊው ነገሩን በመቀጠል እርሱ ተለይቷቸው ሲሄድ ትኩር ብለው እርሱን ሲመለከቱት ሳሉ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆመው ስለምን ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ትቆማላችሁ ይህ ከእናንተ ተለይቶ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ሲያርግ እንዳያችሁት እንዲሁም ይመጣል ሲሉ በዕርገቱ ብቻ ሳይወሰኑ የዳግም ምጽአቱን ጨምረው አስረድተዋቸዋል ።

ከዚህ ላይ ሁለት ሰዎች የተባሉት በቁሙ ሁለት ሰዎች ሳይሆኑ መላእክት ናቸው ። ይኸውም መላእክት መሆናቸው የሚታወቀው ከዕርገቱ አልፈው እንደዚሁም በኋላ ሲመጣ ታዩታላችሁ ብለው መናገራቸው ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤ በኋላ እስከዓረገበት ቀን ድረስ ለደቀ መዛሙርቱ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ቦታዎች ይታያቸው እንደ ነበር ቅዱስ ቃሉ ይመሰክራል ።

መላእክትንም ሰዎች ብሎ መጥራት በመጽሐፍ ቅዱስ የተለመደ ነው ፡ ለምሳሌ ሰዶምንና ገሞራን ሊያጠፉ ከእግዚአብሔር ታዘው የመጡት መላእክት ወደ ሎጥ ቤት ሲገቡና ሎጥም በእንግድነት ሲቀበላቸው በሰው አምሳያ እንጂ መላእክት ናቸው ተብሎ እንዳይደለ ፡ ቃሉ እንዲህ ሲል ይገልጻል ሁለቱ ሰዎች ሎጥን አሉት ከዚህ ሌላ ማን አለህ አማችም ቢሆን ፡ ወንድ ልጅም ቢሆን ፡ ሴት ልጅም ብትሆን ፡ በከተማዪቱ ያለህን ሁሉ ከዚህ ሥፍራ አስወጣቸው እኛ ይህንን ሥፍራ እናጠፋለንና ዘፍጥ ፲፱-፲፪ ።

ይህንን ልንጠቅሰው የፈለግነው ዕርገትን የሚመለከት ሆኖ ሳይሆን መላእክት ሰው ተብለው እንደሚጠሩ ለማስረዳት ያህል ነው ።

በሌላም በኩል ከላይ እንደ ተገለጸው መላእክት ባይሆኑ ኑሮ ይህ ወደ ሰማይ ሲወጣ ያያችሁት እንደዚሁም ዳግመኛ በክበበ ትስብእት በግርማ መለኮት ሲመጣ ታዩታላችሁ ብለው ባልተናገሩም ነበርና ነው ።

ስለዚህ ዳዊት ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ ብሎ በትንቢቱ የተናገረውንና እግዚአብሔር ወልድም ደቀ መዛሙርቱ እያዩት ያረገበትን ቀን በማስታወስ እነሆ ትንሣኤ በዋለ በ፵ ቀን በየዓመቱ ስናከብረው ቆይተናል ለወደፊትም በዚሁ መልክ ስናከብረው እንኖራለን ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ



# ዜና ሊቃውንት

## የአለቃ በዛብህ አጭር የሕይወት ታሪክ

አለቃ በዛብህ ወንድም ከአባታቸው አቶ ወንድም ከእናታቸው ወ/ሮ ዘይት በ፲፰፻፸፰ ዓ/ም በጐንደር ሀ/ስብከት ደብረ ታቦር አውራጃ እስቴ ወረዳ መሐልጌ ጽዮን መሐል ተራራ ከምትባል ቀበሌ ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከተወለዱበት ደብር መምህር ስለነበሩ የወላጆቻቸውን ቤት ሳይለቁ ከፊደል ጀምሮ የቃል ትምህርትን ፀዋትወ ዜማን በሚገባ አጠናቀው ተምረዋል ። ከዚያም በኋላ የሊቃውንት ምንጭ ወደሆነው መካነ ኢየሱስ ሄደው የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳንን ትርጓሜ የሃይማኖተ አበውን የቁርሎስን ፡ የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ ። ባሕረ አሳብን ቅኔ ጽሕፈትን ተምረው ላልተማሩት ለማስተማር ከሚችሉበት ደረጃ ደርሰዋል ።

በንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ዘመነ መንግሥት የደብረ ታቦር መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያንን አለቅነት ተሹመው እያስተዳደሩ ሐዲሳትን የሃይማኖተ አበውንና የቁርሎስን ትርጓሜን በማስተማር በርከት ያሉ ደቀ መዛሙርትን አስተምረው በማሠልጠን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ።

አለቃ በዛብህ ወንድም በብልህነታቸውና በትምህርታቸው በብዙ ሰዎች ዘንድ እጅግ በጣም የታወቁና የተወደዱ ሊቅ ስለነበሩ ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ወደከፋ ክፍለ ሀገር ተሹመው በሄዱ ጊዜ ሊቀ ካህናትና እንደራሴ አድርገው ይዘዋቸው ሄደው ነበር ። ከዚያም በኋላ ወደ ጐንደር ክፍለ ሀገር ተዛውረው ሲሄዱ አሁንም አለቃ በዛብህን እንደራሴና ሊቀ ካህናት አድርገው ወስደዋቸው ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ እስኪሞቱ ድረስ በታማኝነት አገልግለዋል ።

ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ሙተው ራስ ጉግሣ ወሌ ሲሾሙ በአለቃ በዛብህ ወንድምና በራስ ጉግሣ መካከል አለመግባባት ተፈጠረና አለቃ በዛብህ ጐንደርን ትተው ወደ አዲስ አበባ መጡ ።



አለቃ በዛብህ ወንድም

አዲስ አበባም እንደመጡ ብፁዕ ዕጨጌ አቡነ ሣዊሮስ ማኅደረ ስብሐት ልደታ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ የከተማ ቦታ ሰጥተዋቸው ። በዚያ ጉባኤ እየሄዱ ይኖሩ ነበር ። አለቃ በዛብህ ከንግሥት ዘውዲቱ ጋርም ይተዋወቁ ስለነበር በቤተ ክርስቲያን በኩል አንዳንድ ችግር በገጠመ ጊዜ ከሊቃውንቱ ጋር በመሆን አስፈላጊውን መፍትሄ እንዲሰጡ ይደረግ ነበር ይባላል ።

አለቃ በዛብህ ወንድም ከላይ እንደተጠቀሰው ዕጨጌ ወጳጳስ አቡነ ሳዊሮስ በሰጧቸው በልደታ ቤተ ክርስቲያን ቅጽር አጠገብ ባለው ቦታ የጸሎት ቤት አሠርተው ለብዙ ጊዜ ከኖሩ በኋላ እንደገና የጸሎት ቤቱን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመለወጥ የመድኃኔ ዓለምን ጽላት አስገብተው ቤተ ክርስቲያኑን ለሚያገለግሉ መናንያን ዓለም መነኮሳት ድርጎ አውጥተውላቸው ይኖሩ ነበር ። ከብዙ ጊዜ በኋላ ይህ ቤተ ክርስቲያን ሐውልተ ስምዕ መድኃኔ ዓለም ተብሎ እንዲሠየም አድርገዋል ።



ይህ ለሕዝበ ክርስቲያን መማፀኛ ሆኖ የኖረውና ወደፊትም የሚኖረው ሐውልተ ስምዕ መድኃኔ ዓለም ከ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ወዲህ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ደብረ መድኃኒት ተብሎ ሲሠየም ቤተ ክርስቲያኑም ሰፋ ብሎ እንዲሠራ በታቀደው መሠረት አሁን በመሠራት ላይ ይገኛል ።

ቤተ ክርስቲያኑ ከተመሠረተ ፵፪ ዓመት ሁኖታል ። አለቃ በዛብህ ወንድም በታው ሰፋ ብሎ እንዲሰጣቸውና ቤተ ክርስቲያኑ በዘመናዊ ፎርም እንዲሠራ ፈቃዳቸው አልነበረም ። በርከት ያለ ገንዘብ ተሰጥቷቸው ቤተ ክርስቲያኑ በስፋት እንዲሠራ መንግሥት ራሱ አስቦ ነግሯቸው ነበር ይባላል ።

አለቃ በዛብህ ግን የመንግሥት ገንዘብ አላስገባበትም፡ በራሴው ሀብት በመድኃኔ ዓለም ፈቃድ ነው ቤተ ክርስቲያኑ ሊሠራና ሊስፋፋ የሚችለው የሚል ቃል ከመመለሳቸውም ሌላ ይልቅስ መንግሥትን የምጠይቀው ለፍቼ ደክሜ የሠራሁትን ቤተ ክርስቲያን ማንም እንዳያፈርስብኝ መልካም ውሳኔ እንዲተላለፍልኝ ነው ብለዋል ።

ይህንንም በማለታቸው እንዳንተ ያሉ በቤተ ክርስቲያናችን ሦስት አራት ሰዎች በተገኙ ምነው ? ተብለው ተመስግነው ከመሠረቱት ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ማንም እንዳይደርስባቸው ተብሎ ተወስኖ ውሳኔው በጠ/ቤተ ክህነትና በመታሰቢያቸው ሐውልተ ስምዕ መድኃኔ ዓለም ገዳም ይገኛል ።

አለቃ በዛብህ ጧት ተነሥተው ጉባኤ ሳያሆዱ ሌላ ሥራ አይጀምሩም ነበር አለቃ በዛብህ ወንድም ከሚፈጽሟቸው

ገድልና ትሩፋት እንዱ እንደ አንድ እቃቢ ሆነው ግብር ማድቀቃቸው ሲሆን ሌላው ደግሞ በየወሩ የመድኃኔ ዓለም ዕለት የሚዘከረውን ዝክራቸውን በሚያዘጋጁበት ጊዜ እንደ አንድ ሴት ሆነው መሥራታቸው ነው ።

ቦታው የንፍሮ ገዳም ስለነበረ በየወሩ መድኃኔ ዓለም ሊያስቀድስ ለመጣው ሕዝብ ሁሉ ንፍሮውን ለማሳተፍ ያደርጉት የነበረው ተልዕኮ ለብዙዎች ትምህርትን የሚሰጥ ታላቅ ቁም ነገርን ያዘለ ነበር ።

በዚሁ ገዳም የመድኃኔ ዓለም ዕለት የተቀቀለውን ንፍሮ በልተውና የንፍሮውን ውሀ ጠጥተው የሚፈወሱ ምእመናን ቁጥቅቸው ብዙ ነበር ። አሁንም ብዙ ሕሙማን ይፈወሳሉ ።

አለቃ በዛብህ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ 21 ዓመት ሆኖአቸዋል ። ከላይ እንደተጠቀሰው ቤተ ክርስቲያኒን ሰፋ አድርጎ ለማሠራት በታሰበው መሠረት የእርሳቸውንም አስከሬን በአዲስ ሳጥን ለማስቀመጥ ታስቦ መቃብራቸው በተከፈተ ጊዜ በአማረና በተወደደ መዓዛ ተሞልቶ ከመገኘቱም ሌላ ሣጥኑ ምንም ሳይነካ ሥጋቸውና አጥንታቸው እንደቅባ ኑግ እየወዛ ተገኝቷል ። ይህንንም የቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች ቀሳውስትና ዲያቆናት መዘምራንና አግንያን በሚገባ ተመልክተውታል ።

ሊቀ አለቃ በዛብህ ወንድም በማስተማርና በማስተዳደር ቤተ ክርስቲያናችንን ያገለገሉ መሆናቸው ከሕይወት ታሪካቸው ለመረዳት ይቻላል ። “ሕንፃ ወውሉድ የዓብዩ ስመ” ተብሎ በቅዱስ መጽሐፍ እንደተነገረው አለቃ በዛብህ ያስተማሯቸው ደቀ መዛሙርትና በመድኃኔ ዓለም ስም ያሳነፁት ቤተ ክርስቲያን ስማቸውን ሲያስጠሯቸው ይኖራሉ ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ልዩ ልዩ የሆኑ መንፈሳውያን አገልግሎቶቹን ፈጽመው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን ሊቃውንት አትዘነጋቸውም ። ስማቸውን በታሪክ ዓምድ መዝግባ ለተከታይ ትውልድ ታስተላልፋለች ሁላችንም የአባቶችን የሕይወት ታሪክ በማንበብ ብቻ መላ ዘመናችን ማሳለፍ አይኖርብንም የእኛም ስም በታሪክ ዓምድ ተመዝግቦ ለሁልጊዜ ለመኖር እንዲችል በሚሞተው ሥጋዊ ሕይወታችን የማይሞት ታሪክን አስመዝግበን ለማለፍ መጣር ይኖርብናል ።

የዜናው አቅራቢ አባ ምሕረቱ ይመር

# የግንቦት ልደታ ንፍሮ ከምን መጣ ?

የግንቦት ልደታ ንፍሮ ከምን መጣ ብሎ ከመጠየቅ በፊት ቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደችበት ዕለት ንፍሮ ተቀቅሎ ነበር ወይ ? ይህን የመሰለውንስ ባሕል በዚያን ዘመን የነበረው ሕብረተሰብ ይፈጽመው'ነበርን ? በሀገራችንስ መቼ ተጀመረ ማን ጀመረው ? በርዕሱም እንደተገለጠው ከምን መጣ የሚለውን በቅደም ተከተል ለአንባብያን ለመግለጽ እሞክራለሁ ።

ዜና አይሁድ ወይም የአይሁድ ኅብረተሰብ ታሪክ እንደሚናገረው የአይሁድ ኅብረተሰብ ይገዛ የነበረው በሮም መንግሥት ጥላ ሥር በመሆኑ ነፃነት አልነበረውም ። ይኸውም ግማሹ ነፃነት ፈላጊ በመሆን ከሮም መንግሥት ጋር ሲዋጋ የቀረውም በስደት ላይ ነበር አንዳንዱም በወሕኒ ቤት ታስሮ ይማቅቅ ነበር ። እያቄምና ሐናም ነፃነት ከሚፈልጉት ሰዎች መካከል ስለነበሩ ቁጥራቸው ከስደተኞቹ ጋር ነበር ። ቅድስት ድንግል ማርያምም የተወለደችው በ፩ሺ፬፻፹፰ ዓ. ዓለም ግንቦት አንድ ቀን ሲሆን የተወለደችውም ሊባኖስ በሚባለው ስፍራ በስደት ላይ መሆኑን ታሪኩ ያብራራል ሊቁ ያሬድም በድጓው ከሊባኖስ ሙሽራ ትወጣለች ሲል ዘምሯል ።

ታሪኩ እንደሚለው ለምሳሌ በአይሁድ ኅብረተሰብ ዘንድ ማንኛውም ሰው ሲወልድ ንፍሮ የመቀቀል ባሕል ስለሌለ እመቤታችንም ግንቦት አንድ ቀን ስትወለድ ንፍሮ አልተቀቀለላትም ። ይልቁንስ በጣም የሚያሳዝነው በዚያን ዘመን የአሪቱ ሕግ በሴቶች ላይ ታላቅ ተጽዕኖ ስለነበረው ሴቶች ሲወልዱ ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው ለብቻቸው ዳስ ቢጤም ይሠራላቸዋል ። ምግብም እየተሠራ አንድ ሰው እየወሰደ ይጥልላቸዋል የሚመገቡትም ምግብ ድሆች ለሆኑት ገንፎና አጥሚት ሀብታም ለሆኑት ደግሞ ሥጋና ከነመረቅ ይሰጣቸው ነበር ። እንጂ ንፍሮ የመቀቀል ልማድ ድሮም አልነበር ። ከሰባት ቀን በኋላ ግን ወደቤተሰባቸው እንዲቀላቀሉ ይደረጋል ።

ታዲያ እመቤታችን ቅድስት ድንግል በተወለደችበት ዕለት የግንቦት ልደታ ያልተቀቀለ ከሆነ መቼ ተጀመረ ማን ጀመረው የሚለውን ደግሞ እንመርምር መቼ የሚለውን ጊዜና ዓመተ ምሕረት ተለይቶ ባይታወቅም የመጣበት ምክንያቱና ማን እንደጀመረው ከምን እንደመጣ እንገልጻለን ።

የቅድስት ድንግል ማርያም ልደት በጣም እየታወቀና እየተከበረ የመጣው መስቀሉን ለመፈለግ ወደኢየሩሳሌም የወጣች ንግሥት ዕሌኒ የክርስቶስን መስቀል ፈልጋ ካገኘች በኋላ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ሠራች ። በኢየሩሳሌም የሚገኙትም ምእመናን ግንቦት አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው የእመቤታችንን የልደቷን በዓል በጸሎት ካከበሩ በኋላ ንፍሮ በመቀቀል ሳይሆን ዳቦና ቆሎ አቅርበው ሲመገቡ አየች ። ንግሥት ዕሌኒም ወደሀገርዋ ስትመለስ በሀገር የሚገኙት ክርስቲያኖች በየዓመቱ ግንቦት አንድ ቀን የእመቤታችንን የልደቷን በዓል እንዲያከብሩ አስተማረች ይባላል።ከዚያም ቀጥሎ በአራተኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ የግብፅ ሴቶች ግንቦት አንድ ቀን በየዓመቱ በቤተ ክርስቲያን እየተሰበሰቡ የልደቷን በዓል ከየቤታቸው ዳቦ እያመጡ እየበሉ በዓሉን ያከብሩ እንደ ነበር የኅብረተሰብ ታሪክ ይናገራል ።

የግንቦት ልደታ በዓል አከባበርም ወደ ኢትዮጵያ የገባው በዚሁ ዘመን ነው ይባላል ። ያመጣውም አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ነው እየተባለ ይነገርለታል ።

የግንቦት ልደታም በዓል እስከ አሥራ አራተኛው ክፍለ ዘመን አፄ ዘርዓ ያዕቆብ እስከ ነገሡበት ጊዜ ድረስ በጸሎትና በቅዳሴ በማኅሌትም ጭምር ሲከበር እንደቆየ አበው ይተርካሉ ። ለግንቦት ልደታ ንፍሮ መቀቀል የተጀመረው በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው ይህንንም አምልኮ ጣዖትና ስለጥንቆላ በሚለው አፄ ዘርአ ያዕቆብ በጻፈው መጽሐፍ ተጽፎ እናገኘዋለን ።

ሁኔታውም እንዲህ ነበር ፣ በየጊዜው ፈልሰው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት አይሁዳውያን ባህላቸውን ይዘው ነው የገቡት ከባህሎቻቸውም ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ከግብፅ ባርነት በሚወጡበት ጊዜ ከሞተ በኩር እና ከመቅሠፈት እንዲድኑ በማለት በጉን አርደው ሥጋውን በልተው ደሙን የቤታቸውን መዝጊያና ጉበኑን እንዲቀቡት ከእግዚአብሔር ታዘው ነበር ። ይህንን በማድረጋቸው ቀሣፊው መላክ ደም የተቀባውን ቤት እያለፈ በመኼዱ የአይሁድ ኅብረተሰብ ከታዘዘው ሞተ በኩርና መቅሠፍት ድኖ ነበር ። የበጉን ደም ቤታቸውን ያልቀቡት ግብፃውያን ግን በመቅሠፍቱ አልቀዋል ። ዘጸ. ፲፪፡፩-፲፫ ።

ደሙን የቤታቸውን መዝጊያ እንዲቀቡ የታዘዙትም ለአንድ ጊዜ ብቻ እንጂ ዓመትና ወር ጠብቀው እንዲቀቡ አልነበረም ። ሆኖም የፋሲካ በዓል የነፃነት በዓል እንደመሆኑ መጠን በየዓመቱ ወሩን ጠብቀው እንዲያከብሩት መታዘዛቸው እርግጥ ነው ። እነሱ ግን ባህል አድርገው በመያዝና ከመቅሠፍት የሚድኑ እየመሰላቸው የሚያርዱትን የፋሲካ በግ ደም የቤታቸውን መዝጊያ መቅባታቸውን እንደልምድ አድርገው ተያያዙት በየጊዜው ወደ ሀገራችን የገቡትም የአይሁድ ኅብረተሰብ ይህንን ልማድ ለኢትዮጵያ ኅብረተሰብ አለማመዱት በመጀመሪያም ይህ ነገር የተፈጸመበት ወር ሚያዝያ ስለነበር ሕዝቡም የሚያዝያንና የግንቦትን ወር እያያዘ መፈጸሙን ቀጠለ ። በይበልጥም የግንቦትን ወር በጣም አድርጐ ለዚህ ተግባር መፈጸሚያ መረጠው ።

ይህ መጥፎ ተግባር ጥቂት በጥቂት እያለ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ በሰባተኛው ክፍለ ዘመን የጨለማው ዘመን እየተባለ በሚጠራውና የዓረቦች ኃይል መስፋፋት በጀመረበት ወቅት የሀገራችን ሕዝብ ያልነቃና ትምህርት ያነሰው በመሆኑ ጠንቋዮችና ዛር አንጋሾች ከላይ የጠቀስነውን አይሁድ በየጊዜው ያመጡትን አጉል ባህል መነሻ በማድረግ በግንቦት ወር መልክ ያለውን በግ እዛፍ ሥር አርደህ ሥጋውን ጠብሰህ ካልበላህ ደሙንም ካልረጨህ ፣ ንፍሮ ቀቅለህ ካልበላህ ንፍሮውንም በእጅ ዘግነህ ራቅ ወዳለ ቦታ የበላው ሁሉ ሄዶ በትኖ የተመለሰ እንደሆነ ከታዘዘው መቅሠፍት ሁሉ ልጁም አዋቂውም ይድናል ። ጉንፋን እንኳን አይዘውም በሽታውም ንፍሮ ወደአልተቀቀለበት ቦታ ተላልፎ ሕዝቡን ይፈጀል እያሉ ይህን መሰሉን መጥፎ ባህል ከኅብረተሰቡ ጋር አቆራኙት ። ኅብረተሰቡም ሳይወድ በግድ በፍርሃት እየለመደው ሄደ ። እነሱም እንደ አምላክ ሆነው ይሰገድላቸው ጀመር፣ ሳይሠሩ ቁጭ ብለው ኅብረተሰቡ የደከመበትን ላቡ የፈሰሰበትን የመበዝበዝ እድል ገጠማቸው ።

በዚህ ሁኔታ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ እስከነገሡበት ዘመን ድረስ በየዓመቱ በግንቦት ወር በየዛፉ ስር በየአድባሩ መልክ ያለው በግ ሲታረድ ንፍሮ እየተቀቀለ ሲበላ ፣ ቂጣ እየተጋገረ ቆሎ እየተቆላ በየሜዳው ሲበተን ቆየ አፄ ዘርዓ ያዕቆብም ይህንን ለማስቀረት ሊቃውንቱንና መኳንንቱን ሰብስቦ ካማከረ በኋላ አዋጅ አወጀ አጥፊዎቹንም ቀጣ ጠንቋዮቹንም አሠረ የጥንቆላ መጻሕፍቶችንም አቃጠለ ነገር ግን ይህ መጥፎ ባሕል ሥር ሰዶ ስለነበር ቅጣቱ ሊያግደው አልቻለም ።

አፄ ዘርዓ ያዕቆብም ብልህ መሪ ስለነበር ሌላ ዘዴ ፈለገ ፣ ይኸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅድስት ድንግል ማርያምን በጣም እንደሚወድ ስለሚያውቅ በየዓመቱ የግንቦት ልደታ ሴቱም ወንዱም ሽማግሌውም አሮጊቱም በየአቅራቢያው ባለው ዛፍ ስር እየተሰበሰበ ካለው የእህል ዓይነት እያዋጣ ንፍሮ ቀቅሎ በግ አርዶ ይብላ ካህናቱም ተገኝተው ከመበላቱ በፊት በሰማዕታት ስም አንድ ላይ ቢመገቡ ፍቅር ያስገኝለታል ካህናትም የንስሃ አባት የሆኑት ሁሉ ለአማኞች ይህንን እንዲያስተምሩ እንደአዘዘ ከላይ በጠቀስነው መጽሐፍ ተጽፎ ይነገራል ። ይህም ሁኔታ ቀስ በቀስ እየተለመደ ሄደና ለአምልኮ ጣዖት ይደረግ የነበረው መጥፎ ድርጊት በመልካም ሁኔታ ተለውጦ ለግንቦት ልደታ ንፍሮ እንዲቀቀል የሆነበት መንገዱ ይህ ነው ። የተጀመረውም በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ሲሆን አመጣጡም ይህን በመሰለ ሁኔታ ነው ።

አመጣጡ ይህ ከሆነ አሁንስ የግንቦት ልደታ ንፍሮ በዘመናችን ምን ይመስላል የሚለውን ደግሞ እንመረምራለን። ለግንቦት ልደታ በየዓመቱ በዛፍ ስር ንፍሮ ይቀቀላል በግም ይታረዳል። እነዚህም መጥፎ ተግባሮች የሚፈጸሙበት ምክንያት ጠንቋዮችና ቃልቾች ያልነቃውን ኅብረተሰብ ይህ የግንቦት ወር የበሽታ ወር ስለሆነ ደም ካላፈሰስ



www.ethiopianorthodox.org

# መንፈስ ቅዱስ እንደ (እሳት) ነፋስ

የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ በኃጥአን ሸንጎ ከመቅረቡ ከመስቀሉ ከሞቱና ከመነሣቱ አስቀድሞ ለመረጣቸውና ለሚከተሉት ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን የሚልክላቸው መሆኑን ደጋግሞ አብሥሮአቸው ነበር ።

"የምትወዱኝ ከሆነ ትእዛዜን ጠብቁ እኔም ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር የሚኖረውን አጽናኙን መንፈስ ቅዱስን ይልክላችሁ ዘንድ ፡ አብን እለምነዋለሁ ፤ እርሱም ዓለም የማያየው የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው ። እናንተ ግን ከእናንተ ጋር ስለሚኖርና በውስጣችሁም ስለሚሆን ታውቁታላችሁ ። ዮሐ ፲፬. ፲፭-፲፱ ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም በማለት ተስፋውን ከነገራቸው በኋላ "እኔ እናንተን እንደ ወደድኋችሁ እናንተም ርስበርሳችሁ ትፋቀሩ ዘንድ አዝዣችኋለሁ" በማለት ፍቅር መመሪያቸው ምልክታቸው እንዲሆንም ልኳቸዋል ፤ እርስ በርሳችሁ ከተፋቀራችሁ ሁሉም የእኔ የደቀ መዛሙርት መሆናችሁን ያውቃል ብሎአቸዋል ።

አያይዞም ዓለም እንኳ ቢጠላችሁ አስቀድሞ እኔን እንደጠላ እወቁ ፡ ከዓለም ወገን ብትሆኑ ዓለም በወደዳችሁ ነበር ፡ ዓለም ወገኖቹን ይወዳልና ካላቸው በኋላ ቀጥሎም እውነት እላችኋለሁ እኔ ወደአብ ብሄድ ይሻላችኋል ፡ እኔ ካልሄድሁ በቀር አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ወደ እናንተ አይመጣምና ፡ እኔ ከሄድሁ ግን ይልክላችኋል ። አሁን ልትሸከሙት አትችሉም፤የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት መንገድ ሁሉ ይመራችኋል ። እሱ የሚናገረው ከራሱ ሳይሆን ከእኔ ተቀብሎ ነውና በማለት መንፈስ ቅዱስ መጥቶ በእነሱ ላይ እንደሚያድርና ትክክለኛውን መንገድ እንደሚመራቸው ነግሯቸው ነበር፡ ዮሐ. ፲፮. ፲፪-፲፭ ።

በአይሁድ እጅ በኃጥአን ሰዎች ሞት ተፈርዶበት ከተሰቀለ ከሞቱና ከተነሣ በኋላም እንዞ አሁን የአባቴን ተስፋ እልካለሁ ። እናንተ ግን ከሰማይ ኃይል እስክትለብሱ መንፈስ ቅዱስ እስኪያድርባችሁ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ አትውጡ) አላቸው ሉቃ 24 ፡ በዚህም ትእዛዝ መሠረት ከኢየሩሳሌም ሳይወጡ የጰንጠቆስጤን በዓልንም ለማክበር በተሰበሰቡበት አዳራሽ ውስጥም ሳይወጡ የጰንጠቆስጤን በዓልንም ለማክበር ከተሰበሰቡበት አዳራሽ ውስጥም ሳይወጡ እንደአውሎ ነፋስ የመሰለ ድምፅ ድንገት መጣና የተሰበሰቡበትን አዳራሽ መላው ፡ የተከፋፈሉ የእሳት ላንቃዎችም ታዩአቸው በያንዳንዳቸው አደሩባቸው ሁሉም ኃይል በሚሆናቸው መንፈስ ተሞሉ ። እያንዳንዳቸውም በልዩ ልዩ ቋንቋ ይናገሩ ጀመር ። በዚህ ጊዜ በአይሁድ ዘንድ ታላቅ ድንጋጤ ሆነ ። ብዙዎቹ አይሁድ ሐዋርያት በማያውቁት ቋንቋ ሲናገሩ በመስማታቸው ያደንቁ ጀመር ፤ ሌሎቹም እነዚህ ጉሽ ጠጅ ጠጥተው የሆነ ያልሆነውን ይቀባጥራሉ በማለት ይሳለቁ ጀመር ። በዚህ ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ጋር ሆኖ በድፍረት ተነሣና የሚከተለውን ስብከቱን በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ በተሰበሰበበት አዳራሽ ቁሞ መስበክና ማስተማር ጀመረ ። የሐ. ሥራ ፪. ፲፬ ።

እናንት የይሁዳ ሰዎች በኢየሩሳሌም የምትኖሩ ሁሉ እስቲ ስሙ ጊዜው ገና ጧት ሦስት ሰዓት ነው ፡ እንዴት በመንፈስ ቅዱስ ተመልተው የሚናገሩትን ሰዎች ሰክሩ ትለዋቸዋላችሁ? ይህ ነገር ቀድሞ ሲል በነብዩ በኢዩኤል የተነገረ አይደለምን ሥጋን በለበሰ ሁሉ ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ ፤ (አሳድራለሁ) ፤ ወንዶች ልጆቻችሁና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ ፤ ጕልማሶቻችሁና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፤ ጕልማሶቻችሁ ራእይን ያያሉ፤ሊቃውንቶቻችሁ ሕልምን ያልማሉ ፤ በወንዶቻችና በሴቶች በሮቼ ላይ መንፈሴን አሳድራለሁ።ትንቢትም ይናገራሉ ተብሎ አልተነገረምን?..."በማለት ማስተማርና መገሠጽ ጀመረ ። ጴጥሮስና ወንድሞቹ ሐዋርያት ጌታ ኢየሱስን ጠልተው ተመቅኝተው በመስቀል ከገደሉ የአይሁድ ማኅበር መካከል ቆመው ስለኢየሱስ አምላክነት (የእግዚአብሔር አብ ልጅነት በድፍረት ማስታማር እንዴት ቻሉ ? ለሚለው ጥያቄ ሰፊ ቦታ የሚኖረውን ያህል ሰፋ ያለና ጥራት ያለው ትክክለኛ መልስ አለው ። የአይሁድ ፋሲካ ባለፈ በአምሳኛው ቀን በሚከበርበት በጰንጠቆስጤ በዓል በተሰበሰቡበት አዳራሽ እንደአውሎ ነፋስ ድምፁን እያሰማ ከመግባቱና የተከፋፈለ የእሳት ላንቃ በያንዳንዳቸው ራስ ላይ ከማረፉ በፊት ይህን የክርስቶስን አምላክነት መመስከሩ ቀርቶ የርሱ ተማሪዎች መሆናቸውን እንኳ መናገር እንደማይደፍር ጌታ በተያዘ ጊዜ ጴጥሮስ ተጠይቆ የሰጠው መልስ በቂ ይሆናል ፤ ጌታ በተያዘ ጊዜም ሐዋርያት አይሁድን ከመፍራታቸው የተነሣ ቤት ዘግተው ተቀምጠው እንደነበረ የጌታ የትንሣኤ ታሪክ ያረጋግጣል ። ጌታም ይህን ስለሚያውቅ ነበር።ከሰማይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ ከኢየሩሳሌም አትውጡ" ያላቸው መንፈስ ቅዱስ ሳያድርባቸው ስለጌታ ኢየሱስ አምላክነት እናስተምራለን ብለው ቢሞክሩ ከስሕተት ላይ ይወድቁ ነበርና ፤ አጽናኝ መንፈስ ቅዱስ ስላላደረባቸው ይፈሩና ይጠራጠሩ ነበርና ነው ።

መንፈስ ቅዱስ ካደረባቸው በኋላ ግን ፈሪዎች የነበሩ ደፋሮች ሆኑ ፡ አላዋቂዎች የነበሩ አዋቂዎች ሆኑ የሙሴንና የነቢያትን ትንቢት እየጠቀሱ ለማስረዳት ብቁዎች ሆነው ተገኙ።ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ "የእስራኤል ሰዎች ሆይ ይህን ነገር ስሙ እግዚአብሔር በከሀሊነቱ በተአምራቱ በድንቅ ሥራው የገለጠላችሁ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው ። እናንተ ጠልታችሁ ተመቅኝታችሁ አሳልፋችሁ በኃጥአን እጅ ሰጣችሁት ፤ ሰቀላችሁት ፤ ገደላችሁትም እግዚአሪሔር ግን የሞትን ማሠሪያ ፈቶ ከሙታን ለይቶ አስነሣው ፤ ሞት እሱን ሊይዘው አይችልምና ......ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ እንደሚነሣ ነፍሱም በሲኦል እንደማትቀር መፍረስ መበስበስ እንደሌለባት ዳዊት አስቀድሞ ተናገረ ። እርሱንም እግዚአብሔር አስነሣው እኛ ሁላችንም ምስክሮቹ ነን ........ ። በማለት ቀጥተኛ ምስክርነቱን በድፍረት ሰጠ ። የሐ. ሥራ ፪. ፭-መጨረሻ ።

በዚህ ጊዜ በአዳራሹ የነበሩት ሕዝበ አይሁድ ልባቸው ተሰበረ ፤ ምን እናድርግ በማለትም ሐዋርያትን ጠየቁ ፤ ጴጥሮስም በናዝሬቱ በኢየሱስ ስም እመኑ ንስሐ ግቡ ተጠመቁ አላቸውና ወዲያው ሦስት ሺህ ያህል ሕዝብ ተጠመቁ መንፈስ ቅዱስ አደረባቸው ።

ቀድም ሲል መጥምቁ ዮሐንስ የንስሐን ጥምቀት ባጠመቀበት ጊዜ እሱ ክርስቶስ እንደሆነ የተጠራጠሩት ሰዎች ነበሩና ትክክለኛውን ምስክርነቱን ሲሰጥ "እኔ መንገድ ጠራጊ የእሱን ጐዳና አስተካካይ እንጂ ክርስቶስ አይደለሁም ። ስለዚህም እኔ በውሃ አጠምቃለሁ ከእኔ በኋላ የሚመጣ ፤ የጫማውን ማዘቢያ (ጠፍር)ስንኳ መፍታት የማይቻለኝ ክርስቶስ ግን በውሀና በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል" በማለት የተናገረው ትንቢት በዚህ ጊዜ ተረጋገጠ ። ሐዋርያት በእሳትና በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ ፤ እነሱም ሌላውን አይሁዳዊና አረማዊ ሳይለዩ በእሳትና በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቁ ጀመር ። የሐ. ሥራ ፰. ፲፭-፲፯ ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፍርሃት የሚሉ ነገር ከሕሊናቸው ስለተወገደ ዓለምን በመከፋፈል በአረማውያን ሀገር እየተዘዋወሩ ሲያስተምሩ መንፈስ ቅዱስ በአማኞቹ አሕዛብ ላይ ሲያድርባቸው ይታይ ነበር ፤ ለሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን አዳራሽ እንደ ነፋስ ድምፁን እያሰማና እንደተከፋፈለ የእሳት ላንቃ እየታየ የወረደው መንፈስ ቅዱስ በአማንያንና በእውነተኞች ተነሳሕያን እያደረ ነው ። በንስሐ ለማይመለሱ ግን አይጠጋቸውም ።

እንደአውሎ ነፋስ ተጠቅሎ ፡ እንደ እሳት ላንቃ ተከፋፍሎ ትልቁን አዳራሽ በሞላው ጊዜ በአዳራሽ ውስጥ በተገኘው ሁሉ ላይ አላደረም ፡ ከላይ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሐዋርያትና (መቶ ሃያ ቤተ ሰብእ) በልዩ ልዩ ቋንቋ ሲናገሩና የክርስቶስን አምላክነት ሲመሰክሩ ሌሎቹ ግን ይዘብቱ ነበር ። አለመታደል ነው ።

አሁንስ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚቀልዱ ስንቶቹ ናቸው ? አሁንም መንፈስ ቅዱስ በየአንዳንዱ አንባቢ እንዲያድር ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን ።

መምህር ሀብተ ማርያም ተድላ

---

ሀ ንፍሮ ካልቀቀልክ እራስህም ልጆችህም ትታመማላችሁ ሀብታችሁና ንብረታችሁም አይባረክም እያሉ ስለሚያታልሉት ነው የሚታለሉት ። አሁን ግን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በተቻለ መጠን በድንግል ማርያም ስም የሚፈጸም ከሆነ ዛፍ ስር ንፍሮ ቀቅሎ ፡ በግ አርዶ ፤ በጣያት ስም ተሰብስቦ ከመብላት ይልቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስዶ ለተራቡት ማብላትና ለዚያ የሚወጣውን ወጭ ገንዘብ ቤት ንብረት ለጠፋባቸው መስጠት ዋጋ ያለው መሆኑን በማስተማሯ ኅብረተሰቡ ነገሩን እየናቀውና እየተወው በመሄድ ላይ ይገኛል ፤ ስለበሽታውም በጤና ጥበቃ በኩል በየጊዜው ትምህርት ስለሚሰጥና ኅብረተሰቡም ሄዶ እየታከመ ከበሽታው ስለሚድን በሽታ በእግዚአብሔር አምኖ በመጸለይ በመጠመቅ ከዚያም አልፎ በመታከም እንጂ ንፍሮ በመቀቀል እንደማይዳን ገብቶታል ። ስለዚህ ወደፊት በየዛፉ ሥር ንፍሮ መቀቀልና ደም ማፍሰስ በቅርብ ጊዜ ከኅብረተሰቡ አእምሮ እንዲወገድ ተስፋ አለን ። ይህም በተግባር እንዲውል የሁሉንም መተባበር ይጠይቃል ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ





www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

የልማት ሥራ ለሰው ልጅ ታላቅ ጸጋና ከፍ ያለ ክብር መሆኑ እንጀራህን በፊትህ ወዝ ብላ ተብሎ ለመጀመሪያው ሰው በእግዚአብሔር የተሰጠውን ትእዛዝ መመርመሩ በቂ ነው ።

ይህንን የተቀደሰ አምላካዊ ትእዛዝ አብነት በማድረግ በኢትዮጵያ ያሉት ካህናት የክህነት አገልግሎታቸውን ሳያቋርጡና ሳያስታጉሉ በተጨማሪ እርሶ ማምረትም ዕለታዊ ተግባራቸው ፡ነው ካህናቱ እርሻውንና የቤተ ክርስቲያኑን አገልግሎት ሁለቱንም አጣምረው ሲሠሩ መቆየታቸው ፡ አሁንም በዚህ ሥራ እንዳሉ እንገነዘባለን ።

እንዲያውም ባሁኑ ጊዜ ሥራቸውን በማሻሻልና ልማትን በማቋቋም ከፍ ያለ ምርት በማግኘት ተወዳጅነትን ያተረፉ በርከት ያሉ እንዳሉ ሳናስታውሳቸው አናልፍም ልማት ከሚካሄድባቸውም አብያተ ክርስቲያናትና አብያተ ትምህርት መካከል በትግራይ ሀገረ ስብከት በመቀሌ ከተማ በሚገኘው ከሣቴ ብርሃን በመባል በታወቀው ት/ቤት ያለው የልማት ሥራ እንዴት እንደሚካሄድ የከሣቴ ብርሃን ሰላማ የካህናት ማሠልጠኛ ርዕሰ መምህርና የልማት ሥራ ኃላፊ የሆኑትን መምህር ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁን አነጋግረናቸው ነበር ።

1. ትንሣኤ ይህ በከሳቴ ብርሃን ሰላማ የሚካሄደው የልማት ሥራ መቼ ተጀመረ ሥራውን የሚያካሂዱትስ እንዴት ያሉ ሰዎች ናቸው?

መልስ፡- የልማቱ ሥራ የተጀመረው በ፲፱፻፷፩ በሐምሌ ወር ሲሆን ሥራውን የሚያካሂዱትም ሠርቶ ማሳያና ማሠልጠኛ እንደመሆኑ መጠን አብዛኛውን ሥራ የሚያካሂዱት ሰልጣኞቹ ናቸው ። እንዲህም ስንል በሠልጣኞቹ ብቻ ሳይሆን የሀገረ ስብከቱ ሠራተኞችም ከዚሁ ሥራ በመሳተፍ በተቻላቸው መጠን ይሠራሉ ።

ትንሣኤ በልማቱ የሚመረቱ ምርቶች ምን ዓይነት እንደ ሆኑ ቢገልጹልን?

መልስ፡- በዚህ በከሳቴ ብርሃን ሰላማ ት/ቤት የሚመረቱ ምርቶች ፡ 1ኛ/ በገመድ የሚሠራ የሥጋጃ ምን ጣፍ
2ኛ/ በገመድ የሚሠሩ አልጋዎች
3ኛ/ እንደዚሁም በገመድ የሚሠሩ የሳሎን ፎቴ ወምበሮች

በገመድ የሚሠሩ እነዚህ ሲሆኑ በእርሻም በኩል ጤፍ ፡ በቆሎ ፡ ስንዴ ፡ እነዚህን የመሳሰሉትን እናመርታለን ።

በአትክልትም በኩል ቲማቲም ፡ ድንች ፣ ሽንኩርት ፣ ጎመን ፣ ቃርያና እነሱንም የመሳሰሉትን አትክልቶች እየተከልን እንጠቀማለን ። እንግዲህ እነዚህን እየዘራንና እየተከልን ለማልማት የምንጠቀምበት 2 ሄክታር የሚሆን ቦታ አለን በዚህም ለካህናት ዘመናዊ የሆነውን የእርሻ ዘዴ እናስተምራቸዋለን።



መ/ ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ

ትንሣኤ ፡ ከላይ ቢ.ቃጫ ገመድ ዓልጋዎችንና የሳሎን ፎቴ ወምበሮችን እንሠራለን ብለው ነበር ፣ እነዚህን አልጋዎችንና ወምበሮችን የምትሠሩበትን ቃጫ ማን ነው የሚያቀርብላችሁ?

መልስ ፡- ስለ ቃጫ ችግር የለንም በአካባቢያችን ቃጫ በብዛት ስለሚገኝና የአካባቢውም ሕዝብ ቃጫውን እየገመደ (እየፈተለ) ወደ ገበያ ለሽያጭ ስለሚያቀርብ ከዚያ እየገዛን ነው የምንጠቀም እንጂ ሌላ የሚያቀርብልን የለም ።

ትንሣኤ ፡ ለመሆኑ ቃጫው ሕዝቡ የተከለው ነው ወይስ ራሱ የበቀለ ነው?

መልስ ፡- ቃጫው ሕዝቡ የተከለው ሳይሆን ራሱ የበቀለ ነው በተለይ ሽከት በተባለው ቦታ ቃጫ በብዛት የሚገኝበት ቦታ ስለሆነ ሕዝቡ ከዚያ እየሄደ ቃጫውን እየቆረጠና እየገመደ ለሕዝብ በሽያጭ እያቀረበ ይጠቀምበታል ።

ትንሣኤ ፡ ከላይ ከተጠቀሱት ነገሮች ሌላ የምታመርቱት ምርት አለ?

መልስ ፡- አዎ ሌሎችም ብዙ የልማት ሥራዎች አሉን እነዚህም ከዕንጨት የሚሠሩ መስቀል እንሠራለን እንዲሁም ልብስ ተክህኖ ሹራብ እየሠራን ለሽያጭ እናቀርባለን ።

ትንሣኤ ፡ ልብስተክህኖ የሚሰፋበት የልብስ ስፌት መኪና መኖሩ ግልጽ ነው ነገር ግን ሹራብ የሚሠራው በእጅ ሥራ ነው ወይስ በማሽን?

መልስ፡- የሹራብ መሥሪያ ማሽን ስላለን በዚሁ ነው የሚሠራው ትንሣኤ ልብስ ተክህኖውን የሚሰፋው ሰው እንዴት ያለው ነው ቄስ ወይስ መሐይም ሹራብ የሚሠራበትስ ማሽን ከምን አገኛችሁ።

መልስ ፡- ልብስ ተክህኖውን የሚሰፋት መነኩሴ ሲሆኑ ስማቸውም መልአከ ሕይወት ገ/መስቀል ይባላሉ እኚህም መነኩሴ ለመጀመሪያ ጊዜ በከሣቴ ብርሃን ሰላማ በዚሁ ሥራ ከሰለጠኑ በኋላ እንደገና ለሦስት ወር ያህል ወደ አዲስ አበባ ተልከው በጠቅላይ ቤተ ክህነት የስፌት ማሠልጠኛ ሥራውን አጠናቅቀው ስለ ተመለሱ ። የስፌቱን ስራ የሚያካሂዱት እሳቸው ናቸው መልአከ ሕይወት ገ/መስቀል የመኪና ስፌትን ከመሥራታቸውም በላይ ባሁኑ ጊዜ በሀገረ ስብከቱ የሰበካ ጉባዔ ኃላፊ ናቸው ። ሹራብ የሚሠራበትም ማሽን የተገኘው ብፁዕ አቡነ ናትናኤል በትግራይ ሀገረ ስብከት በነበሩበት ወቅት እርዳታ ጠይቀው ነበር ። በጠየቁትም መሠረት በእርዳታ ከተገኘው ገንዘብ ሹራብ የሚሠራበት ማሽን ቢገዛበት ጠቃሚ መሆኑ ስለታመነበት በ8900 ብር ተገዝቶ እንሆ በሥራ እንጠቀምበታለን በተጨማሪም ይህ የሹራብ መሥሪያ ማሽንና በጠቅላላ የልማቱ ሥራ ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የትግራይ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ለጐደለ ማሟያ እንዲሆን ካህናትም ሆኑ ዲያቆናት መዓርገ ክህነት ሲቀበሉ ለካርኒ የሚከፍሉት ሁሉ ለዚሁ ለልማት ሥራ እንዲውል ፈቅደዋል ።

ትንሣኤ ፣ በዚህ በልማት ውስጥ የሚሠሩት ሠራተኞች ደመወዛቸውን ከምን ያገኛሉ?

መልስ ፡- በዚሁ በልማት ሥራ ለተመደቡት ሠራተኞች ደመወዛቸውን የሚከፍለው የሀገረ ስብከቱ ቤተ ክህነት ነው ይሁን እንጂ ከማሠልጠኛውም መጠነኛ ድጎማ ያገኛሉ ።

ትንሣኤ ፡ ከልማቱ ሥራ የሚገኘውን ገቢ የሚቆጣጠረው ማን ነው?

መልስ ፡ ዋና ኃላፊው የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሲሆኑ የሚቆጣጠረውም የልማቱ ማሠልጠኛ የሥራ መሪና የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የሚመድቡት ሰው አለ በጊዜው እየተከታተለ የሚቆጣጠረው እሱ ነው ።

ትንሣኤ ፡ ይህ የከሳቴ ብርሃን ሰላማ የልማት ሥራ ለወደፊት ያለው ዕቅድ እንዴት እንደ ሆነ ሰፋ አድርገው ቢገልጹልን?

መልስ ፡- የልማቱ ሥራ ለወደፊት ያለው ዕቅድ ካህናቱንና ዲያቆናቱን እየሠለጠነ ቤተ ክርስቲያንን በምእመናን እያራቀቀ ካህናቱም ሆኑ ምእመናኑ የሥራ ክቡርነትን ተገንዝበው እጅ ለእጅ ተያይዘው እየሠሩና እርስ በርሳቸው እየተረዳዱ ኑሮዋቸውን አሻሽለው ከመኖራቸውም በላይ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን በማስፋፋትና ስብከተ ወንጌልንም በየአውራጃውና በየወረዳው ለማስራፋት ነው ዕቅዳችን ሲሉ መምህር ኃይለ ሥላሴ አለማየሁ አብራርተውልናል ።

አዎ ሥራ ታላቅ ጸጋና አምላካዊ ትእዛዝ መሆኑን ሁላችን እናውቃለን እንግዲያስ የልማት ሥራ አምላካዊ ትእዛዝ መሆኑን ከተገነዘብን ትእዛዙን አክብረን ወደ ልማት ሥራ መሠማራት ሠርተንም መጠቀም የእኛ ፋንታ ነው ፡ ባንሠራ የምንጐዳ እኛ ነን ብንሠራ ደግሞ የምጠቀመው እኛው ነንና ወደ ልማት ሥራ እንሠማራ ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ

# የቤተሰብ ዓምድ

## በምርጫ የሚፈጸም ጋብቻ

ምርጫ ሲባል የቀለምን የቆዳን ወይም የአጥንት ጥራት እየተባለ የሚጠራውን የዘረኛነትና የጠባብ ብሔርተኛነትን ጠባይ የሚመለከት አይደለም ። የጋብቻ ምርጫ በመልካም ጠባይ ወይም ሥነ ምግባር ላይ የተመሠረተ ሆኖ የአካልና የአእምሮ መመጣጠንን የሚጠይቅ በተለይም ከልባዊ ፍላጐትና ከፈቃድ የመነጨ እንዲሆን ያሻል ።

በሌላ በኩል ከዚሁ በተወረሰ ርካሽና አልባሌ ልማደ ሰብእ ፣ ለምሳሌ እንደ ዛር እንጋሽነት የአቴቴ ጫሌ ማንጠልጠል ወሠራ ገብስማ ቀይ ጥቁር ዶሮ አዳል በግ ፡ ቡሐ በግ ፡ ወዘተ. እያሉ ከሚያምርቱ ቤተሰቦች ጋር ጋብቻ መመሥረቱ ቀርቶ ጉርብትናቸው እንኳ ይጐዳል ። ዘር ከልጓም ይስባል እንዲሉ በጥሩ ትምህርት እስካልታነፁ ድረስ የመተተኞችና የአስማተኞች የጋኔን ሳቢዎችና የቃልቻ ከዳሚዎች ልጆች የወላጆቻቸውን ጠባይ ይተዋሉ ቢባል ድመት መንኩሳ ዐመሏን አትርሳ እንደተባለው ዓይነት ከመሆን አይዘልም ።

ይህን በማስመልከት ከቅዱስ መጽሐፍ የምንቀስመው ዕውቀት አለ ። ለምሳሌም አብርሃም በእምነት ተጠርቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከሄደ በኋላ በአገሬ ለምንትና የጅአግራፊ አቀማመጥ ደስ ብሎት ሳለ የአገሬ ኑዋሪ ሕዝብ በሚሠሩት ኃጢአት ረከሳና ተንሳቀላ ባየ ጊዜ ከዚያ ዓይነት ጣኦት አምላኪ ኅብረተሰብ ጋር ተደብልቆ ለመኖር አልፈቀደም ። ሌላው ቀርቶ ለልጁ ለይስሐቅ እንኳ ከዚያች አገር ሴቶች ልጆች መካከል መርጦ ሚስት ለማጋባት አልፈለገም ። ከዚህም የተነሣ አገልጋዩን እያቡርን ጠርቶ ልጄን ይስሐቅን በዚህች ምድር ከሚኖሩ ሴቶች ልጆች ጋር እንዳታጋባው ተጠንቀቅ” ብሎ ካዘዘው በኋላ ወደ አባቶቹ አገር ወደ ሦርያ (መስጴጦምያ) ሄዶ ርብቃ ተብላ የምትጠራውን ውብ ቆንጆ አጭቶ እንዳመጣለት ተጽፎአል ።

ታዲያ አብርሃም ለምን ይህን አደረገ ብለን ብንጠይቅ ከነዓናውያንን የጠላበት ምክንያት በመልካቸው ወይም በጠባያቸው ወይም የካም ዘሮች በመሆናቸው አይደለም ። እርሱ የተመለከተው ትልቅ አስጸያፊና አስከፊ ነገር ዕንጨት ጠርበው ድንጋይ አለዝበው የልዩ ልዩ እንስሳትና አራዊት የባሕር ዓሣዎችንና የሰማይ አዕዋፍን ቅርጽ በማውጣት ማምለካቸውን ለፀሐይ ለጨረቃ ለከዋክብትና ለሌሎችም ፈለክ ፈለካት መስገዳቸውን ነው ። የገዛ ልጆቻቸውን መሥዋዕት አድርገው በማቅረብ ለእሳት ቃጠሎና ለዘንዶ ግብር አድርገው መ



www.ethiopianorthodox.org

ስጠታቸውንም በዓይኑ አይቷል ። ስለዚህም እንደዚያ ካሉት ሰዎች ጋር ጋብቻ መመሥረት የሚያስከትለውን ያሞራል ውድቀትና የእምነት መዛባት አውቋል ።

እኛስ የምንኖርባት ዓለም ከዚያ ዓይነት የባዕድ አምልኮ ልምድ የነፃች ስለመሆንዋ ማረጋገጫ አለ ወይ? ያን ጊዜም ድንጋዩንም ሆነ ዕንጨቱን ጠርበው አለዝበው በማለስለስ ብዙ ተደክሞበት በተወሠነ የአምልኮት ሥፍራ በማኖር ነበር ፤ የሚሰግዱለት ዛሬ ግን በቀላሉ ቅዳሜ የተገዛ ጀበና እሁድ ተሚሸቶ ስኛ ቡና በሚፈላበት ጊዜ ቄጠማ ተጐዝጉዞ ጽጌረዳ ተረፍርፎ ቢቻልም ሽቱ ተርከፍክፎ ሱቲ ተጐናጽፎ ጫት እየተቃመ ፤ ዕጣን እየተጨሰ ራሱን በክስልፍም ለማያድነው ሽክላ ክብር ተሰጥቶት የፀ[?]በናው አምላክ እየተባለ አማን አውለን ፤ ቸር አውለን ፤ እየተባለ ይማረትበታል ። በተለይም ከግንቦት መባቻ ወር ጀምሮ እስከ አመሠላሳ በየዛፍ ሥር ንፍሮ በመቀቀል ቂጣ ፤ ቆሎ አዘጋጅቶ አርዶ እርስ በርስ መገባበዝና ለአድባር ለአውጋር (ለዛፍና ለተራራ) ስዕለት መሣሉ እንደቀጠለ ነው ።

በሃይማኖት ትምህርት በጋዜጣና መጽሔት ኅትመት ቢመከር ቢዘከር ሁሉም የገዘሆን ጆሮ ይስጠኝ በማለት እምቢ ማለቱ ታውቋል ። መፍትሔውስ? ቢባል "አውቆ የተደበቀ ቢጠሩት ወይ አይልም" እንዲሉ ካሁን በኋላ ሁሉም እየወቀ በሚሰራው በደል ራሱ የሚጠየቅበት እንጂ ሌላ ዋቢ የሚጠራበት ጉዳይ አይደለም ።

ታዲያ ይህን ዓይነት አስጸያፊ የባዕድ አምልኮ ልምድ የሚከተሉ የሰይጣንን ሠራዊት በቂጣ ቆሎ የሚያባብሉ ሁሉ ልጅ ሲወልዱ ወልደን ለቃልቻ እናስታቅፍ እያሉ ችግር ስለሚፈጥሩ እንዲህም ያሉትን የልማድ እሥረኞች መጀመሪያ ከዚህ አደገኛ እግር ብረት ከመላቀቃቸው በፊት በጋብቻ ሊዛመዱዋቸው እንደማይገባ ያልተረዱ ይኖሩ ይሆን??

ተወደደም ተጠላም እዚህ ላይ የጋብቻ ምርጫ ማድረግ በግድም በውድም አስፈላጊ ነው ። የእግዚአብሔር ቃል "እንደነዚህ ካሉት መካከል ተለዩ ከመታላቱ የእምነት ሰው ነህምያም ባትርከሱ" ይላልና (፪.ቆሮ.፮.፲፯-፲፰።)

ታላቁ የእምነት ሰውየ ነህም ያም ባዕድ አምልኮ በጋብቻ ላይ የሚያስከትለውን ጠንቅ ሲገልጥ "ሰሎሞንን የሚያህልና እርሱን የሚመስል ንጉሥ በምድር ላይ አልተነሣም ነበር ። ዳሩ ግን በባዕድ አምልኮ የተመረዙ የውጭ አገር ሴቶች በኃጢአት ገመድ ጐትተው ወደሚወድቅበት አዘቅት ጣሉት ይላል ። ከወንዶችም ወገን ቢሆን ሚስቶቻቸውን በዚህ ዓይነት ችግር ላይ የጣሉ ብዙዎች ስለሆኑ ጋብቻን በሚመለከት ጉዳይ ጥሩ ምርጫ ከማድረግ መቦዘንና ዘልሎ መዘፈቅ ተገቢ አይደለም ከዚህም ሌላ የምንሰጠው አስተያየት አይኖርም ።

"ተግሣጽ ለሰው ጠባይ ሲሆነው እራሚ፡መናገር ከንቱ ነው ካልተገኘ ሰሚ፡ ሲል ባለቅኔው እንደተናገረ ሆኖ ቀረ እንጂ ከዚህ ይበልጥ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ሊቃውንት ሰፊ ምክር ሰጥተውበታልና ነው ።

አቶ ከበደ ሚካኤልም በቅኔያቸው
ልማድ ድንቁርና አንድነት ተባብረው
ባሪያ እያደረጉ ይገዙታል አሥረው
ምንኛ ብርቱ ነው ኃይለኛ ጠንካራ
ልማድ የሁሉ ምንጭ ያግር የመከራ ።

ብለውታል ። ስለዚህ ይህን ከመሰለው የመጥፎ ልማድ ሰንሰለት የተላቀቃችሁ እንኳን ደስ አላችሁ በወጣትነት ደረጃ ላይ የምትገኙ ጉብሎችም ወደ ጋብቻ ዓለም በምታመሩበት ጊዜ ሀብተ ስንኩል ጋብቻ ከልክል ከሆነው ከዚህ ዓይነት ባዕድ አምልኮ ነፃ የሆነ ቤተሰብ ለመመሥረት እንድትችሉ እንመኝላችኋለን ። መልካም ምርጫ ለሁላችሁ ።

መ/ አዕ. መክብብ አጥናው



# በዓለ ሃምሳ

በዓለ ሃምሳ በብሉይ ኪዳን ዘመን የመከር በዓል እየተባለ ይጠራ ነበር ።(ዘፀ.፳፫-፲፯) ሃምሳ ቀን ተብሎ የተቆጠረውና የተጠራውም ከፋሲካ ጀምሮ ነው ፋሲካ ማለትም በእብራውያን ቋንቋ "አለፈ" ማለት ሲሆን በኛ ደግሞ ማዕዶት ማለት ነው ። የእስራኤል ልጆች በግብፅ አገር ሳሉ በግ አርደው ደሙን በደጃፋቸው በመርጨት ከአምላክ ቁጣ ለመዳን ችለዋል ። መልአኩ ሠይፉን መዞ በበግ ደም የተረጨውን ቤት እየየ አልፎ ስለሄደ ዕለቱን ፋሲካ (አለፈ) ብለውታል ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም እስራኤላውያን በየዓመቱ ማለት ከግብፅ የወጡበትን ቀን በሚያከብሩበት ዕለት የሚታረደውን በግ "በግዓ ፋሲካ" እያሉ ሲጠሩት ኑረዋል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ሳምንት የፋሲካ ሳምንት ነበረ ። እርሱም ንጹሕ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ደሙን ስላፈሰሰልንና በበጉ ደም ፈንታም በራሱ ደም ከኀጢአታችንና ከበደላችን ሁሉ ስላነፃን "ፋሲካችን ክርስቶስ ስለኛ ታርዶአልና" ተብሎ ተጠርቶአል ።

በዓለ ሃምሳ በሐዲስ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ ወርዶበታል ከፍ ብለን እንደጠቀስነው ከትንሣኤ ክርስቶስ ጀምሮ ቢቆጠር ሃምሳ ቀን ይሆናል ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለአይሁድ በትእዛዝ የተሰጡ በዓላት ሰባት ናቸው እነርሱም በሳምንት አንድ በዓመት ስድስት ሲሆኑ አንድ ሌላ በዓል ደግሞ በመቃብያን ዘመን የተጨመረ አለ ። በዓላቱን በዝርዝር ለመረዳት ቢያስፈልግ ።

1ኛ/ ዕለተ ሰንበት (ዘሌዋ ፳፫፡፪)

2ኛ የቂጣ በዓል (በዓለ ናዕት እስራኤላውያን ከግብጽ የወጡበት (ዘፀ ፲፪፡፩-፳

3ኛ/ በዓለ ሰዊት (የመከር በዓል) በዓለ ሃምሳ ወይም በዓለ ጰንጠቆስጤ(ዘፀ ፳፫ ፳፮-፴፭)

4ኛ/ መለከቶች የሚነፉበት ቀን (የቀንደ መለከት ድምጽ የሚያሰሙበት (ዘሌ ፳፫፡፳፫-፳፭)

5ኛ/ በዓለ መጸለት (የዳስ በዓል) ወይም የአዝመራ ክታች (ዘሌ. ፳፫፡፴፱-፵፫)

6ኛ/ አይሁድ ከእግዚአብሔር ይቅርታ የሚጠይቁበት (የማስተሰረያ ቀን )እርሱም የደስታ በዓል ተብሎ የሚጠራው (ዘሌ. ፳፫፡፳፮-፴፪)

7ኛ/ ፋሪም ይህም በአስቴር ዘመን አይሁድ ከጠላቶቻቸው ዕረፍት ያገኙበት (አስቴር ፱፡፲፮-፳፰)

8ኛ/ የመቅደስ መታደስ መታሰቢያ በዓል ይህም ከአራትና ከነቢያት በኋላ በመቃብያን ዘመን ተጀመረ የብሉይ ኪዳን እምነት የሚከተል ሁሉ ቀዳሚት ሰንበትን ለማክበር ይገደዳል ። ደግሞም ወንዶች ሁሉ በቂጣ በዓል ፡ በበዓለ ሃምሳ ፣ በዳስ በዓል በቤተ መቅደስ እንዲገኙ በጥብቅ ታዘዋል ።(ዘዳግ.፲፮፡፲፮)

ከነዚህ ታላላቅ በዓላት ውስጥ በዓለ ሃምሳ ወይም በዓለ ጰንጠቆስጤ ብለን የጠቀስነው ሲሆን ይህም በዓል እስራኤላውያን ከግብፅ ወጥተው ወደ ከነዓን ከገቡ በኋላ የሀገራቸውን በረከት በመቅመሳቸው ምክንያት በየዓመቱ የሚያከብሩት በዓል ነው ። በዚሁ ዕለት በየዓመቱ የእስራኤል ዘር ሁሉ ከአዝመራው አንዳንድ ነዶ እየያዘ ወደ ካህኑ ይቀርብና ካህኑም ጸሎተ ቡራኬ ያደርስለት ነበረ ። ከሰባት ሱባኤ በኋላም እንደገና ከምድራቸው ፍሬ ወስደው መሥዋዕት በማቅረብ የተቀደሰ ጉባኤ ያደርጉ ነበር (ዘፀ ፳፫፡፲-፲፱)

በዓለ ሃምሳ ከዚሁ ዘመን ጀምሮ በዚህ ሥርዓት ሲሠራበት ቆየ ይህን በዓል ለማክበርም በየዓመቱ የአይሁድን እምነት የሚከተል ሕዝብ ሁሉ ከየአገሩ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄደ ያከብር ነበር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባረገ ባሥረኛው ቀን የዚሁ በዓል ቀን ነበር ስለሆነም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከማረጉ በፊት ደቀ መዛሙርቱን ሰብስቦ "እኔ አንድሄድ ይሻላችኋል ፣ እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣም እኔ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ" ከማለቱም ሌላ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አስጠንቅቆ "ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ ፡ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ' አላቸው ። (ዮሐ. ፲፮፡፯ ።የሐ.ሥ.፩፡፬-፭

ሐዋርያት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል በመጠበቅ በማርቆስ እናት በማርያም ቤት በጸሎት ይተጉ ነበር ። በበዓለ ሃምሳው ማለት ጌታችን ባረገ ባሥረኛው ቀን ከጐረቤት አገሮችና ከሩቅ አሕጉሮች የመጡ ሰዎች በኢየሩሳሌም ከተማ በብዛት ይታዩ ነበር ። ኢየሩሳሌም የዓለም አማካይ ሥፍራ ከመሆንዋም በላይ የታሪክ የእምነትና የሥልጣኔም መዲና ነበረች ስለዚህ በዚያን ጊዜ የሰዎች በእየሩሳሌም መገኘት በተለያየ ምክንያት እንደነበር ይነገራል ። ቀደም ብለን እንደጠቆምነው አኩሌቶቹ በእምነት ምክንያት በዓሉን ለማክበር መጥተዋል ። አንዳንዶቹ ደግሞ የኢጣልያ መንግሥት ፍልስጥኤምንና ጐረቤቶችዋን ሁሉ በቅኝ ግዛት ይዞአቸው ስለነበረና ችሎትም ያስችል የነበረው በዚሁ አማካይ ሥፍራ በኢየሩሳሌም በመሆኑ በልዩ ልዩ ክርክርና በይግባኝ ስም የመጡ ሰዎችም ነበሩ ። ኢየሩሳሌም የንግድ መነሃሪያ ስለነበረችም ንግዱ ለማትረፍ ከሩቅ የመጡ ጥቂት ነጋዴዎችም በዚሁ አጋጣሚ ተገኝተዋል። ከአይሁድ ወገን የሆነ ኢየሱስ የሚባል በዕንጨት ላይ ተሰቅሎ ሙቶ ከተቀበረ በኋላ ተነሥቶአል ይባላልና ሄደን ነገሩን እናጣራ እያሉ ከሩቅ የመጡ አንዳንድ ሰዎችም ነበሩ የሰሎሞንንና የሌሎቹ የዕብራውያን ጠበብትን ታሪካዊ ሥራ አይተው ለማድነቅና ዝናንም ወደ ሀገራቸው ለመውሰድ የመጡ ሰዎች እንደነበሩም በአፈ ታሪክ ሲነገር ይሰማል ።

ኢየሩሳሌም በነዚህ ሁሉ ተሞልታ በምትጨነቅበት ወቅት ሐዋርያት በማርያም ቤት ሳሉ "ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ ቤቱንም ሞላው እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው ፣ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር" (ዮሐ ሥራ ፪፡፩-፬)

እነሆ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማይታበል ቃሉ "መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ" ባለው መሠረት በዚሁ ዕለት ተፈጸመ ። ሰዓቱ ከቀኑ ገና ሦስት ሰዓት ያህል ነበር ። አብዛኛው ሕዝብ የነበረው በቤተ መቅደስ ነው ነገር ግን በዚያች ወቅት በኢየሩሳሌም ከተማ ይህ የሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ መታደስና መጐልመስ ዳር እስከ ዳር ተሰማ ሕዝቡም ከየሥፍራው ወደ ማርያም ቤት ይሮጥ ጀመር ሰዎቹም ሐዋርያት የሚናገሩአቸውን ቃላት እየሰሙ እጅግ መደነቅ ያዛቸው በተለይም ከተለያዩ አገሮች የመጡ ሰዎች ሐዋርያት በቋንቋቸው ሲናገሩ ሰምተው እኩሌቶቹም እየተገረሙ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ በማድነቅ ክብርና ምስጋና ለፈጣሪ ሲያቀርቡ ሌሎቹ ደግሞ ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥተው ጠግበው ነው አሉ ። (የሐ.ሥ ፪፡፭-፲፫)

በዚህ ወቅት ቅዱስ ጴጥሮስ ሰዓቱ ገና ጠዋትና በሀገሩ ወግና ልማድም የወይን ጠጅ ለመጠጣት ፈጽሞ የማያስችል ወቅት መሆኑን ለፌዘኞቹ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ከመስጠቱም በላይ ይህም ምሥጢር አስቀድሞ በነቢዩ በኢዩኤል የተነገረው ቃለ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ በሐዋርያት ላይ የወረደው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሆነ አስረዳቸው ። ከዚህም በማያያዝ አይሁድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የፈጸሙትን በደል ከማስተዋል የራቀ መሆኑንና ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ቀደም ብሎ በነቢዩ በዳዊት የተነገረውን ቃለ ትንቢት ተንትኖ ቢያስረዳቸው ወደል



www.ethiopianorthodox.org

ባቸው ተመልሰው በሠሩትና በተናገሩ ት ሁሉ እግዚአብሔርን መበደላቸውን ስላረጋገጡ“ወንድሞች ሆይ ምን እናድ ርግ ብለው የጸጸት ጥያቄ ሐዋርያትን እ ንደጠየቁ ተጠቅሶአል ። ቅዱስ ጴጥሮስ ም የእያንዳንዳቸው ኃጢአታቸው ይሠ ረይ ዘንድ ንስሐ መግባት እንደሚያስ ፈልጋቸው ቢያስታውቃቸው በዕለቱ አምነው ንስሐ ገብተው የተጠመቁ ሰ ዎች ቁጥር ሦስት ሺህ እንደሆኑም ተመ ዝግቦአል (የሐ.ሥ. ፪፡፴፩)

እነሆ በዚህ ዕለት በተጠቀሰው ሰዓ ት ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ጸጋ ስለተገ ኘበት የርደተ መንፈስ ቅዱስ ቀን ይባላ ል ከጥንታዊ በዓል ከበዓለ ሃምሳም ጋር አንድ ቀን በመዋሉ በዓለ ሃምሳ በዓለ ጰ ንጠቆስጤ ተብሎ ሲታሰብ ይኖራል ከ ዚህም በላይ ይህ ቀን የቤ/ክርስቲያን ልደ ት ይባላል።ቤ/ክርስቲያን የክርስቶስ ደ ቀመዛሙርት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በለበሱበት ዕለት በነበሩና ከልዩ ልዩ አ ገሮች በመጡት ሰዎች አማካይነት ጭ ምር የተስፋፉች ስለሆነች የቤ/ክርስቲ ያን ልደት (መሠረት) ይህ ዕለት መሆኑ ተረጋግጦአል (የሐ.ሥ.፲፩፡፳፮)

ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ታድሰው በዕውቀት እስከ ጉለመሱ ድረስ ፍሩ ሃን ነበሩ ከዚህ በኋላ ግን ጥቡአን ሆኑ ፡ ድንጉጻን ነበሩ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በድ ፍረት ተሞሉ እስከ ሞት ድረስም የወን ጌልን መከራ ተሸክመው ወደ ዓለም ሁሉ ሄዱ በየአደባባዩ በእምነት ተሞል ተው የወንጌልን ቃል በማስተማራቸው ና በመመስከራቸውም በተቃዋሚዎቻ ቸው ተይዘው ተደበደቡ ፡ እንደበግ አ ረዱአቸው እንደጉመንም ቀረደዷቸ ው ፡ቆዳቸውንም እንደ እንስሳ ገፈጡ በ አሸዋ ሞልተው እያሸከሙ በየስፍራው አዞሩአቸው ። ከአንበሳና ከነብርም ጋር አታገሉአቸው ሥጋቸው እየተቦጫጨ ቀ ሲወድቅና ደማቸው እንደጎርፍ ሲፈ ስ ደስ ይላቸው ነበር ።

ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ተመሥርታ በብዙ መሥዋዕትነትም በዓለም ሁሉ ተ ስፋፍታ እነሆ ከእኛ ዘንድ ደርሳለች በ ሀገራችን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያናችን ተጀምሮ እስ ከተፈጼረሰ ድረስ በሐዋርያት ላይ የደረሰ ውን መከራ ያህል በመምህራኖችዋና በ ሊቃውንቶችዋ ላይ አልፎ አልፎ መፈ ጸሙ አልቀረም ይልቁንም በአብያተ ክ ርስቲያኖቻችን ሕንፃዎችና በቅርሶቹ ላይ ብዙ ምዝበራና ወረራ ደርሶአል ። ይህም በተለያየ መንገድና በተለያየ ዘ መናት መፈጸሙን ከታሪክ ለመረዳት እንችላለን ይኸውም አንደኛ ከሀገራቱ ውስጥ እንደግራኝና ጉዲት የመሳሰሉ በ የዘመናቱ ተነሥተው የፈጸሙት በደል ሁለተኛ አንዳንድ እምነት ቢሶች አስመ ሳይ ካህናት ቅርሶችን እየሰረቁ በስውር ለባዕዶች እየሸጡ ወደ ውጭ በማስወጣ ታቸው ሲሆን ሌላው ደግሞ የውጭ ወ ራሪ ኃይል እንደ ቱርክ ፣ ግብፅና ኢጣል ያ የመሳሰሉት ሀገራችንን በተለያየ ዘመ ናት አመቺ የሆነ ጊዜያትን እየተንተራ ሱ ወደ ሀገራችን በመግባት አብያተ ክ ርስቲያኖቻችንና ንዋያተ ቅድሳቶቻች ንም ሁሉ አቃጥለው መጻሕፍቶቻችን ም ቆነጻጽለው ብዙ የታሪክ ሥፍራዎች ን አበላሽተውብናል ከባድና አሳዛኝ በደልም አድርሰውብናል ይህም ማንም ኢትዮጵያዊ ምንጊዜም የማይረሳው በ ደል ነው ።

ትምህርታችንን ለማጠቃለል ያህል ወደ ዋናው መሠረተ ሀሳብ እንመለስና ስለ በዓለ ሃምሳ ወይም ስለ በዓለ ጰንጠ ቆስጤ ሰዎች በዘመናችን በምን ዓይነ ት ሁኔታ እንደሚያከብሩት በእንዴት ዓይነት መልክ እንደሚመለከቱት እን መርምር።አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች ይ ህን በዓል ከእብራውያን ባልተለየ ሁኔ ታ ያከብሩታል ። ጥቂቶቹ ደግሞ እንደ ፈዝና እንደቀልድ አድርገው ይጠሩታ ል ። በተለይም እኛ በመንፈስ ቅዱስ ተ ጠምቀናል ሌላው ክርስቲያን ነኝ የሚ ለው ግን በመንፈስ ቅዱስ ስላልተጠመ ቀ ክርስቲያን ነኝ ሊል አይገባውም ይ ላሉ ።

ሐዋርያት የተለያዩ ቋንቋዎች ተገል ጸውላቸዋል የሚለውን ቃል ተንተርሰ ውም ሀብተ ቋንቋ ተሰጥቶናል እያሉ በተ ሰበሰበው ሕዝብ መካከል ቆመው የወፍ ጫጫታ በሚመስል ጩኸት ያጭበረብ ራሉ የየት አገር ቋንቋ ነው ? ሲሏቸውም የሰዎች አይደለም የመልአክት ቋንቋ ነው ፤ እያሉም ያታልላሉ ። በመሆኑ ለ ሐዋርያት የተገለጠላቸው ቋንቋ የታወ ቀውና ሰዎችም በየሀገራቸው ሲነጋገሩ በት የነበረ የጳርቴ ፡ የሜድ ፡ የኢላሜጤ የቀጰዶቅያና የጳንጦስ የእስያና የፍርግ ያ የጵንፍልያና የግብጽ የሌብያና የሮሜ የቀርጤስና የአረብ ወዘተ... አልነበረ ምን? ታድያ እነዚህ ደግሞ ሀብተ ቋንቋ ተሰጥቶናል ካሉ የሌሎች አገሮች ቋንቋ ይቅርና በሀገራችን ውስጥ ካሉት የተለ ያዩ ቋንቋዎች እንኳ ለምን በአንዱ አይ ናገሩም?

ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ “ለአንዱም ትንቢትን መናገር ፡ ለአንዱም መናፍ ስትን መለየት ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር ለአንዱም በልሳኖች የተ ነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል” ብሎ በጻፈው ቃል የቀሆችን ያታልሉበታል በውኑ ጳውሎስ ፍጹም በማይናገሩት ቋ ንቋ ራሳችሁ ፈጥራችሁ ሰዎችን አታል ሉ ሲል ነው ይህንኑ ቃል የተናገረው ? እንደሐዋርያው አባባልስ ከሆነ ከልዩ ወገኖች የታወቀ ቋንቋና ተናጋሪው ፍጹ ም የማያውቀው ቋንቋ ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተገልጾለት ሲናገር ሁለተ ኛውም እንዲሁ አንዱ የተናገረውን የ ታወቀ ቋንቋ ትርጉም ለተሰበሰቡት ሰ ዎች በቋንቋቸው የሚያስረዳ ማለቱ ነ በር እንጂ ሰዎች በተንኮል የተፈጠረ ቋ ንቋ ፈጥረው እንዲናገሩ አልነበረም ።

ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በተለያዩና በ ሰዎች ፈጠራ በተገኘው አዲስ ያልታ ወቀ ቋንቋ ሳይሆን በእውነት ለእውነት በምንነጋገረው ቋንቋ ለማያውቁት ሰዎ ች በቋንቋቸው ተርጉሞ ማስተማር ማለ ት እንደሆነ መገንዘብ ይገባናል እንጂ በተመሳሳይ መንገድ ራሳችን ተሳስተን

ሌላውን ከማሳሳት ብንቆጠብ መልካም ነው ። ከእውነት በራቀ መንገድ መንፈ ስ ቅዱስን መሣሪያ ለማድረግ መሞከር በራስ ላይ ሰይፍን እንደመምዘዝ ያስቆ ጥራል መንፈስ ቅዱስን እንደመስደብ ም ያህል ነው ፤ በዚህ መንገድ የሚደፋ ፈር ሰው በቅዱስ መጽሐፍ “ኃጢአት ና ስድብ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል መን ፈስ ቅዱስን የሰደበ ግን አይሠረይለት ም” ተብሎ የተነገረው ቃል እንዳይ ፈጸምበት የበዓለ ሃምሳን ትርጉም በተ ገቢ መንገድ ማክበር ይኖርበታል (ማቴ ፲፪፡፴፪ ።)

ሊ/ትጉሐን ገብረ ክርስቶስ ኃ/ማርያም



# አጭቃን ኪዳነ ምህረት ወደ ጥንት ደብርነቷ ተመለሰች

## ዘግይቶ የደረሰን ዜና

በጐንደር ሀ/ ስብከት በደብረ ታቦር አውራጃ እስቴ ወረዳ የምትገኘው አጭ ቃን ኪዳነ ምሕረት በብፁዕ አቡነ መር ቆሬዎስ የሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አሳሳቢነ ትና በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማ ኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ መልካም ፈቃድ ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. ተደብ ራለች በዚህ ጊዜ ደብሯ ደብረ ገነት ተ ብላ ስትሠየም የደብሯ አስተዳዳሪ የሚ ሆነው አለቃም መልአከ ገነት እየተባለ እንዲጠራ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክ ለ ሃይማኖት ስለተፈቀደ በአጥቢያው የሚኖሩ ምእመናን ከፍ ያለ ደስታ የ ተሰማቸው መሆኑን ዜናው አስረድ ቷል ።

በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያኑን ለማደስ የሰበካው ሕዝብ ቀደም ሲል በበጎ ፈቃዱ ተነሣሥቶ አስተዋጽኦ በ ማድረግ ጣራውን በቆርቆሮ ስለአስከደ ነው በዓሉ ግንቦት ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ. ም. እጅግ በጣም በሚያስደስት ሁኔታ የተከበረ መሆኑ ታውቋል ።

ዜናው ስለ በዓለ ክብካቡ ሲያብራራ ግንቦት ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. በዙሪያ ው ያሉት የአድባራትና የገዳማት አለቆ ችና አበምኔቶች መምህራን ቀሳውስት ና ዲያቆናት መዘምራን ተጠርተዋ ል። በበዓሉ ዋዜማ ቁጥራቸው በርከት ያለ ካህናት ተገኝተው ስብሐተ እግዚአ ብሔር ሲያደርሱ አድረዋል ። ሥርዓተ ቅዳሴው ከንጋቱ ላይ እንደተፈጸመ ከ ማርገጃው ላይ ድንኳን ተተክሎ “ዝኒ ኩነ በፈቃደ እግዚአብሔር” የሚለው አንገርጋሪ ተመርቶና ተለዝቦ ከተሸበሸ በበኋላ፩ኛ/ሊቀ ኀሩያን እስጢፋኖስ ዋ ጋዬ የሀ/ስብከቱ ዋና ፀሐፊ ። ፪ኛ/ ሊቀ ካህናት ኃይሉ የወረዳው ሊቀ ካህናት ስለደብሯ ቀደምትነትና ታሪካዊነት ከ መግለጻቸውም ሌላ ምን ጊዜም ቢሆን የድጓ መምህር ተለይቷት የማታውቅ በቅዳሴም በስብሐተ ነግህም ዘወትር አገልግሎት የሚፈጸምበት ታላቅ ደብ ር መሆኗን በሰፊው በማብራራት በዓሉ ን ለማክበር ለተሰበሰቡት ምእመናን ከማስረዳታቸውም ሌላ ጥንትም ደብር እንደነበረችና አሁንም በብፁዕ ወቅዱ ስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ መልካም ፈቃድ መደበሯን በማረጋገጥ እያንዳንዳቸው ሰፋ ያለ መ ግለጫ ሰጥተዋል ።

ቀጥሎም የታሪኩ መግለጫ በደብተ ራ እንየው ወርቁ ሲነገር ግጥም ደግሞ በገላው እያሌው ተነቧል ። በርከት ያሉ ቅኔዎችም ከልዩ ልዩ ሊቃውንት ተበር ክተዋል ። ከተበረከቱት ቅኔዎች ጥቂቶ ቹ የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ/ መወድስ ቅኔ ከመልአከ ገነት ሐዲስ ጌታሁን የዚሁ ደብር አስተዳዳሪ

እምርጉቅስ ርእይዋ ወተአምኅዋ ለደ ብረ ገነት ከነዓን ምእመናን ወካህናት ት እስመ ደብረ ገነት ከነዓን ሙሐዘ

አንቅዕት ክብራት

ወእንዘ ፍኖታ ፍኖተ ጽድቅ ይዕቲ ለዘ ይሴፈዋ ታድኅን እሞት

ውሉደ አብርሃም አበዊነ አምጣነ

ባቲ አደው እሞት ውስተ ሕይወት ።

ለዓለም

እምርጉቅሂ ታስተርኢ ከመ

ማኅቶት

ግብረ ጠፈራ ሰማያዊ እስመ ጠፈረ

ጽድቅ ወሃይማኖት

እንዘ ትሠረገው ዘንተ ልብሰ

ቅድሳት

የማነ መርቆሬዎስ ትቀውም

ንግሥተ አድኅኖ ደብረ ገነት

፪ኛ መወድስ ፡

ላዕለ ደብረ ገነት ሰሰለ ጽልመተ

ተትኅቶ ፡ እመ እምተክለ

አብ ተከሥተ መዓርገ አድባር

ዕንቍባሕርይ

ወበዘይመርሕ ግብረ ተፀውኦ ስም

ሠናይ

አስተርአየ ሖልቆልተ ደብርነ

ዘገነት ዕበይ

ወመፍትው ጽዋኤ ስግ አምጣነ

ገነት ደብርነ በተፈጥሮታ ዘተዳግዩ

ለዓለም ፡

ቀርነ ክብርሂ ሶበ አጽምአ ተክለ

ሃይማኖት ኅሩይ

ላዕለ ደብረ ገነት ተጋብአ አዋልደ

ጽዮን መኃልይ

እስመ ተነበየ ቅድመ ወልደሚካኤል

ነቢይ

መዓርገ አድባር መርዓዌ ጽድቅ ከመ

ላዕለ ደብርነ ይትረአይ ።

ደብረ ገነት አጭቃን ኪዳነ ምሕረት ከደጋው

ዝቅ ከቆላው ከፍ ብላ በመሐል እስ ቴ የምትገኝ ስትሆን መሬቷ ወይና ደጋ ጥቁርና ነጣ ያለ አፈር ያለው ነው በ4 ቱ ማዕዘንም አራት ውሃዎች ይፈስሱበ ታል በምሥራቅ በባር ምንጭ በምዕራ



www.ethiopianorthodox.org

ብ ፏፏቴ በደቡብ ዳባ ማጠቢያ አምባ ወንዝ በሰሜን አቤቶ ምንጭ ከታች ጣይ በረድ የተባሉ ከቤተ ክርስቲያኑ ሥር ፈልቀው ወደታች ይፈሳሉ ከዚህም ሌላ በግራና በቀኝ ሁለት ታላላቅ ወንዞች ያዋስኗታል እነርሱም ፩ኛ ዋንቃ ፪ኛ ሳጋ ናቸው ። በእነዚህም ወንዞች ሕዝቡ ለመስኖ አገልግሎት ይጠቀምባቸዋል ። ደብረ ገነት ተብላ እንድትሰየም የተደረገውም አፍላጋቱን በመመልከት ነው ።

የምታበቅላቸው እህሎች፡

ጤፍና ስንዴ አተርና ባቄላ ምስርና ተልባ ገብስና ኑግ ወዘተ ናቸው ። የተተከለችበት ዘመን፡

አጭቃን አሁን ደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት የተተከለችው በ፲፰፻፶፰ ዓ.ም ነው ከተተከለች ፻፳፱ ዓመቷ መሆኑ ነው ። ተከዮቿም የአዛርያስ ድሌ ልጆች ባህፈና ዓመተ ዋህድ ናቸው ። ደብሯን የሚንከባከቡ ለሕዝቡ ዋስና ጠበቃ የሚሆኑ የተጣላ የሚያስታርቁ ደጋግ ሽማግሌዎች ነበሩባት በመንፈሳዊ አገልግሎት በኩልም ብዙ ሊቃውንት ነበሩባት አሁንም ከ፶ የበለጡ ቀሳውስትና ዲያቆናት መዘምራን ይገኙባታል። በአገልግሎትም በኩል በዓቢይ ጾም ጾመ ድጓ በፍልሰታ ስብሐተ ነገህ ይደርስባታል ሰዓታት ይቆምባታል ቅዳሴም ይቀደስባታል፡

አጭቃን ኪዳነ ምሕረት ደብር ሁና ስትኖር በአንዳንድ የግል ጥቅም ፈላጊዎች ተጽዕኖ ገጠር ሆና ቆይታ ነበር ። አብያተ ክርስቲያናት ራሳቸውን በራሳቸው ችለው እንዲኖሩ በተወሰነው ቃለ ዓዋዲ መርሕ መሠረት ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የተወሰደባቸውን መዓርግ እያስመለሱ በተሐድሶና በዕድገት ጐዳና ላይ ይገኛሉ ።

ስለዚህ በብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ የሀ/ስብከቱ አሳሳቢነት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መልካም ፈቃድ ደብሯ ደብረ ገነት ተብላ ተሰይማ የደብሯም አስተዳዳሪ መልአከ ገነት ተብሎ ስለ ተሠየመ በአጥቢያውና በዙሪያው ለሚኖሩት ካህናትና ምእመናን ከፍ ያለ ደስታ ተሰምቷቸዋል ።

ስለዚህም ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ለብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ የጐንደር ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ዕድሜና ጤና በመመኘት ሕዝበ ክርስቲያኑ ያደረገውን ምስጋና ዜናው አስረድቶ አሁንም አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ይህንን ከፍተኛ ክብር በመሻት ላይ ስለሚገኙ አሳባቸው ተሳክቶ ግባቸው ተሟልቶ የተመኙትን ክብር ለመቀዳጀት እንዲችሉ ለቅዱስነታቸው ረዥም ዕድሜ ከጤንነት ጋር ይስጥልን በማለት ዜናው አሳቡን አጠቃሏል ።

የደብረ ገነት አጭቃን ኪዳነ ምሕረት
ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት

# የተቅማጥ በሽታዎች

የተቅማጥ በሽታዎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከፍ ያለ የጤና ችግር ከሚፈጥሩት ዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች ናቸው ።

በየዓመቱ በመቶ ሺ የሚቆጠሩትን የኢትዮጵያ ሕፃናት ገና በለጋ ዕድሜያቸው እንዲቀጩ ከሚያደርጉ በሽታዎች ውስጥ የተቅማጥ በሽታዎች የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛሉ ።

ስለሆነም የተቅማጥ በሽታዎች ጐጂነት ከፍ ያለ እንደመሆኑ መጠን ኅብረተሰቡ እንዲያውቀውና በጥብቅ እንዲከላከለው ያስፈልጋል ።

ዋና ዋናዎቹ የተቅማጥ በሽታዎች የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ የአሜባ ተቅማጥ በሽታ
፪ኛ/ የሺጌላ ” ”
፫ኛ/ የኮሌራ ” ”

፩ኛ/ የአሜባ ተቅማጥ በሽታ፡

ይህ በሽታ እያጣደፈ አንዳንዴም እያሰለሰ ደምና ንፍጥ የመሰለ ነገር በመደባለቅ የሚያስቀምጥና የሚያስምጥ በሽታ ነው ። የበሽታው መነሻ ኤንትአሜባ ሄስቶሉቲክ የሚባል ፕሮቶዞአ ከሚባሉ ሕዋሳት ወገን የሆነ ሕዋስ ነው ።

በሽታው ሲይዝ የሆድ መታወክና ማቅለሽለሽ፣ ቁርጠት እያጣደፈ ወይም እያሰለሰለ ማስቀመጥ ማስማጥ በዓይነ ምድር ላይ ደም ንፍጥ መሳይ ነገር አንዳንዴም የመግል መታየት የሰውነት መዛል ናቸው ።

የበሽታው መዛመቻ መንገዶች፣

፩ኛ/ የበሽተኛው ዓይነ ምድር በንክኪ በቀጥታ ከእጅ ወደ አፍ ከዚያም ወደ ሆድ ሲገባ ነው ።

፪ኛ/ ዝንብ አሜባ ካለው ሰው ዓይነ ምድር ላይ አርፋ እንደገና በምግብ ላይ ያረፈች እንደሆነና ይኸንንም የተበከለ ምግብ ሌላ ሰው ሲመገበው ነው ።

፫ኛ/ የአሜባ ሕዋስ ባለበት በዓይነ ምድር የተበከለውን ውሃ በመጠጣት፡

፬ኛ/ በአሜባ በሽታ ሕዋሳት የተበከለውን አትክልትና ፍራፍሬ በደንብ ሳያጥቡና ሳያበስሉ በመብላት ነው ።

የበሽታው መከላከያ፣

ሀ/ ዓይነ ምድርን ዝንብ እንዳይደርስበት ሆኖ በደንብ በተሠራ መጸዳጃ ቤት ብቻ መውጣት ።

ለ/ አትክልቶች ፍራፍሬዎችና ሌሎችም ምግቦች በዓይነ ምድር እንዳይበከሉ ከፍ ያለ ጥንቃቄ ማድረግ፣

ሐ/ የዝንቦችን መራቢያ ቦታዎች ማጥፋት፣

መ/ የግልና የአካባቢ ንጽሕናን ማዘውተር፣

ሠ/ ከምግብ በፊትና ከመጸዳጃ ቤት በወጡ ቁጥር እጅን በንጹህ ውሀና በሳሙና ደህና አድርጐ መታጠብ፣

ረ/ በበሽታው የተያዙትን ሁሉ ታክመው እንዲድኑ በአስቸኳይ በአቅራቢያ ወደሚገኘው የጤና ድርጅት ማድረስ፣

፪ኛ የደምና የመግል ተቅማጥ (ሺጉሎሲስ)

ይህ በሽታ አጣዳፊ በሆነ ሁኔታ በመጀመር ደምና መግል የሚያስቀምጥ አደገኛ በሽታ ነው ።

በአጠቃላይ የግልና የአካባቢ ንጽሕና በጐደላቸው ሥፍራዎች የሚገኝ ከፍ ያለ የጤናና የኤኮኖሚ ቀውስን የሚያስከትል ነው ።

የበሽታው መነሻ ምክንያቶች ዓይነታቸው የበዛ ሺጌላ የተባሉ የባክቴሪያ ዘር የሆኑ በጣም ረቂቅ ሕዋሳት ናቸው፣

የበሽታው ምልክቶችም ድንገት ጀምሮ ቶሎ ቶሎ በመደጋገም ደምና መግል የቀላቀለ ተቅማጥ ያስቀምጣል ፡ ቁርጠት አልፎ አልፎ ተውከት ይኖራል የሰውነት ትኩሳት እየጨመረ ይሄዳል ።

የበሽታው መዛመቻ መንገዶች፣

፩. በሕዋሳቱ የተበከለን ውሃ በመጠጣት፡

፪. በበሽታው የተመረዘውን ሰው ዓይነ ምድር በእጅ ነክቶ በደንብ ሳይታጠቡ በመብላት፡

፫. ከበሽተኛው ዓይነ ምድር ጋር ግንኙነት ያደረገች ዝንብ የበከለችውን ምግብ በመብላት፡

የበሽታው መከላከያ ዘዴዎች፡

፩. በበሽታው የተያዘውን ሰው በጥንቃቄ አግሎ በማሳከም በሽታው ባጭሩ እንዲቀጭ ማድረግ፣

፪. የበሽተኛውን ዓይነምድር ጉድጓድ ውስጥ በመቅበር፣

፫. በሽተኛው የሚመገብባቸውን ቁሳቁሶች በፈላ ውሃ ደህና አድርጐ ማጠብ፣

፬. ዓይነምድርን ዝንብ እንዳትደርስበት ሆኖ በተሠራ መጸዳጃ ቤት ብቻ መውጣት፣

፭. ውሃና ምግብን እንዳይበከሉ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ፣

፮. የዝንብ መራቢያዎችንና ዝንቦችን ማጥፋት ።

፫ኛ ኮሌራ፣

ኮሌራ "ቪበሪይ ኮሌራ" በሚባሉ የባክቴሪያ ዘር በሆኑ ሕዋሳት ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው በሽታው በጣም አጣዳፊ በሆነ ሁኔታ የሚያስቀምጥና የሚያስታውክ ሲሆን በፍጥነት የሕክምና ርዳታ ካልተገኘ በሰውነት ውስጥ የሚገኘውን ፈሳሽ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሙጥጥ አድርጐ በመጨረስ ሰውነትን መርዞ ይገላል ።

የበሽታው ምልክቶች፡

፩. በድንገት የሚጀምር አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት፡

፪. በትውከትና በተቅማጥ የሚወጣው ፈሳሽ የሩዝ ውሃ ወይም አጓት የመሰለ ሽታ የሌለው፡

፫. ትውከትና ተቅማጥ በያዘ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሰውነት አለመጠን ይሟሽሻል የዓይኖች መሥረግ ወይም ከዓይን ጉድጓዶች ጠልቀው መግባትና መፍዘዝ ናቸው ።

የበሽታው መዛመቻ መንገዶች፡

፩. በበሽታው ሕዋሳት የተበከለ ምግብንና ውሃን በመብላትና በመጠጣት

፪. ዝንብ በዓይነምድር በበከለቻቸው ውና በደንብ ባልታጠቡ ቁሳቁስ በመመገብ፣

፫. በበሽተኛው ዓይነምድር በተበከለ እጅ ሳይታጠቡ በመብላትና ከበሽተኛው ጋር ንክኪ አድርጐ ሳይታጠቡ በመብላት፡

የበሽታው መከላከያ ዘዴዎች፡

፩. በሽተኛውን በጥንቃቄ አግሎ በፍጥነት ሕክምና እንዲያገኝ ማድረግ፡

፪. የበሽተኛውን ዓይነምድርና ትውኪያ በጥንቃቄ እየተቀበሉ በደንብ መቅበር፡

፫. ምግብና ውሃን በዓይነምድር እንዳይበከሉ ከፍ ያለ ጥንቃቄ ማድረግ ምግብን አብስሎ መብላት ፡ ውሃን አፍልቶና በንጽህና ይዞ ጥቅም ላይ ማዋል።

፬. ዓይነምድርን ዝንብ በማይደርስበት በደንብ በተዘጋጀ መጸዳጃ ቤት ብቻ መውጣት፣

፭. ንክኪ ያደረጉት ሁሉ በሽታውን እንዳያዛምቱ መከታተል፣

፮. የግልና የአካባቢ ንጽሕናን በደንብ መጠበቅ ናቸው ።

ሲ/ር የሺወርቅ ከበደ

## በዝግ ቤት .....

ከገጽ ፳፱ የዞረ

ስለ እርሱም ከሙታን ተለይቶ መነሳት እየተገረሙ በማውራት በመንገድ ሲጓዙ ጊዜው ገና ጨለማ ነበርና ሊያውቁት ስለ አልቻሉ በመካከላቸው ሆኖ ምን ሁናችሁአል በማለት ጠየቃቸው ።

እነቀለዮጳም አንተ ለኢየሩሳሌም ዕንግዳ ሰው ነህን ከሶስት ቀን በፊት በኢየሩሳሌም የተደረገውን አታውቅምን እነሆ ይህ ሶስተኛ ቀን ነው ለእሥራኤል መድኃኒት ይሆናል ብለን ያመንበት ነቢይ ነበር ገረፉት ሰቀሉት ተቀበረም ከዚህ ሁሉ ጋር የሚገርመን አንዳንዶቹ ሴቶች ከመቃብር ሄደው አጣነው አሉን ከሙታን ተለይቶ ተነስቶአል አሉን እያለ ቀለዮጳ ሲነግረው እርሱም በጨለማው ተሰውሮ ዕንግዳ ሰው በመምሰል አየና ጌታስ በሙሴና በነቢያት በመጻሕፍት የተጻፈውን ትንቢት አታነቡም አታስተውሉም እያለ በመከራከር ሲመልስለትና በአጠቃላይ ሲነግራቸው አያስተውሉም ነበር ።

በዚህ ዓይነት እየተነጋገሩ ከኤማሁስ ስሳ ኪሎ ሜትር ወደ ኢየሩሳሌም በመንገዘ ከቤት ሲደርሱ ጨለማውም ስለ አለቀቀ መንገደኛ መስሎአቸው ባለማወቅ ከእኛ ጋር እንደር ሲሉት በድንገት ከመካከላቸው ተሰውሮ ጠፋባቸው ።

እነርሱም ከቤት ገብተው ሳለ የመጽሐፍትም ምሥጢር ተገለጸላቸውና በመገረምና በመደነቅ አይሁድን በመፍራት ቤታቸውን ዘግተው ደቀ መዛሙርቱ ሁኔታውን እያነሱ ሲጨዋወቱ ከመ

ወደ ገጽ ፩ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# የግብርና በረከት

በዛሬው የግብርና በረከት ጽሑፋችን
የምናቀርብላችሁ ከአለፈው የቀጠለ ባ
ለሙያው ይናገር ከሚለው የሰው ሠራሽ
የእንስሳት ማራቢያ ዘዴን የሥራ እንቅ
ስቃሴን የሚመለከት ይሆናል ።


በሰው ሠራሽ የእንስሳት ማዳቀል ዘ
ዴ የተገኙት የተሻሻሉ ዲቃላዎች ወይ
ም ክልስ ከብቶች ከወላጆቻቸው ጋር
ሲነፃፀሩ ያላቸውን ልዩነት ቢአስረዱን
ተብሎ ለባለሙያው ለቀረበው ጥያቄ

ው ከ፪፻፴፮-፪፻፶፱ ኪ. ግራም ሲደርስ ዲ
ቃላዎቹ ግን ከ፫፻፶-፫፻፹ ኪ.ግራም ይ
መዝናሉ ይህም ማለት ለርድ ሲቀርቡ
ይበልጥ የሥጋ ምርት ይሰጣሉ ማለት
ነው ያገር ዝርያ ጊደር ለመጀመሪያ ጊዜ
ጥጃ የምትወልደው ዕድሜዋ ከ፫-፬ ዓ
መት ሲደርስ ሲሆን ዲቃላዋ ጊደር ግን
፫ ዓመት ከመሆንዋ በፊት ልትወልድ
ትችላለች ።

በወተት ምርት በኩልም እጅግ የጐ

ነው ።

ይህ የሰው ሠራሽ የእንስሳት ማዳቀ
ል ዘዴ ሣይንስ በከብት አርቢው ዘንድ
እንዲለመድና ተግባራዊ እንዲሆን ጥረ
ት በሚደረግበት ጊዜ ከገበሬው የሚፈ
ለገው ድርሻ ምን ይሆናል ። ለሚለው
ጥያቄ ባለሙያ ሲመልሱ ከከብት አርቢ
ው የሚፈለገው ድርሻ ማሳደግ ከገበሬ
ው አስተሳሰብና አመለካከት ለውጥ ጋ
ር የተያያዘ ነው ። ይህንን ለውጥ ለማግ



ምርጥ የሥጋ ከብት ኮርማ ዓይነት

ባለሙያው መልስ ሲሰጡ ዲቃላዎች
በወላጆቻቸው ማለትም በሀገር ዝርያ
ዎች ላይ በብዙ አቅጣጫዎች የተሻለ ገ
ናና ባሕርያት እንደሚአሳዩ እስከ አሁ
ን የተካሔዱ ጥናቶች ያረጋግጣሉ ። ከ
እሉ በኋላ ዝርዝር ባለ መልኩም ሲና
ገሩ ፡

ያገር ውስጥ ዝርያ ላሞች ከብደታቸ

ላ ልዩነት ይታያል ። ከሀገራችን ላም
በአንድ የአለበ ዘመን ከ፫፻-፭፻ ሊትር
ወተት ሲገኝ ከአንድ ክልስ (ዲቃላ) ላ
ም ግን ከ፩ሺ.፭፻-፪ሺ ሊትር የሚደርስ
የወተት ምርት ይገኛል ከዚህ የምናጠ
ቃልለው ከ፬-፮ የሚደርሱ የአገር ዝርያ
ላሞች ከመያዝ ይልቅ አንዱ ዲቃላ ላ
ም መያዙ የበለጠ ጠቀሜታ እንዳለው

ኘት እጅግ አስቸጋሪና አድካሚ ቢሆን
ም ለውጡ አይገኝም ማለትም አይቻ
ልም ። በቅድሚያ ሁኔታዎች ተመቻች
ተው መገኘት ይኖርባቸዋል ። በተናጠ
ልም ሆነ በቡድን ማስተማርን ማሳየት
ን ይጠይቃል ። ለምርቱ ተመጣጣኝ ዋ
ጋ የሚአገኙበትን በቅርቡ ይፈልጋል
ዘራቸው ለተሻሻሉ ከብቶችም በቂ የሕ



ክምና አገልግሎት ያስባል ። በሌላ በ
ኩል ደግሞ ዲቃላ ላሞች ካሉት የሀገር
ዝርያ ላሞች የበለጠ የወተት ምርት ስ
ትሰጠውና ከቤተሰቡ ፍጆታ አልፎ ለ
ጐረቤቱ እየተሸጠ መጠነኛ ተጨማሪ
ገቢ ሲያገኝ የከብቶችን ዘር ለማሻሻልና
ድርሻውን ለማሳደግ ይነሣሳል ፣ ይገፋ
ፋል ፣ ዕምነቱንም ያዳብራል ከሳይንስ
ና ቴክኖሎጂ ጋር እንዲተዋወቁ የገበሬ
ዎች የማሰልጠኛ ጣቢያዎችና ተቋሞች
ተቋቁመውላቸው ትምህርት ይሰጣቸዋ
ል ። የልማት ሠራተኞችና አደራጆች
በመካከላቸው ይገኛሉ ።

. ስለሆነም የእንስሳትን ምርታማነት
ማሳደግ በከብት አርቢው የሚጠበቅ ከ
ፍተኛ ድርሻ ነው ። በዚህ በሰው ሠራ
ሽ የእንስሳት ማዳቀል ረገድ ቡድኑ ከተ
ቋቋመ ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ
ምን ያህል ዐበይት ተግባሮች አከናው
ኖአል ። ለሚለው ጥያቄም ሲመልሱ
ቡድኑ በአለፉት ሁለት የዝግጅትና የ
ተግባር ዓመታት ውስጥ ጠቅለል ባለሁ
ኔታ የሚከተሉትን ክንውኖች አካሂ
ዶአል ። በመስክ ክንውን ረገድ እስከ
አሁን ድረስ ማለትም በጠቅላላው
፲፯ሺህ የሚደርሱ ዲቃላዎች ተከናው
ነዋል ። ከ፯ሺሀ-፰ሺህ ጥጆችም እንደ
ተወለዱ ተገምቷል ብለዋል ።

በቃልቲ ኮርማ ጣቢያ ለአባለ ዘር ማ
ምረቻ አንድ ላቦራቶር ከነሙሉ ድርጅ
ቱ ተቋቁሞአል ። የአገልግሎት መስጫ
ጣቢያዎችን ለመክፈት መጠነኛ ጥና
ት ተደርጐአል በአጠቃላይ እንቅስቃ
ሴውን በአስተማማኝ ደረጃ ለመጀመር
ና ለማራመድ ቁሳዊና የቴክኒክ መሠረ
ቱን በመጣሉ አኳያ እስከ አሁን ድረስ
ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል ብለ
ዋል ።

ስለዚህ ይህ ዓይነቱ አሠራር እጅግ
በከፍተኛ ውጥን በመሆኑ በከብት አር
ቢው ገበሬ ዘንድ ሊደገፍና ሊታቀፍ ይ
ገባዋል ። ባለሙያው እንደአስረዱት ከ
አገር ውስጥ ላሞችና ከዲቃላዎች የሚገ
ኘው የወተት ምርት ሲመዛዘን ምን ያ

ህል ርቀት እንዳለው ተመልከተናል ።
ታዲያ ይህ ከሆነ ጥሩ ምርትና የተትረ
ፈረፈ ንዋይ ለማግኘት ይህንን መሰሉን
ሥራ በመተባበር ከባለሙያዎቹ መመ
ሪያ በመቀበል ለተግባራዊነቱ ከፍተኛ
ተሳትፎ ማድረግ ያሻል እንላለን ።

ፍሥሐ ባንተ

# የጻድቁ የአቡነ ዮሴፍ ታሪክ

የታላቁ ጻድቅ የአቡነ ዮሴፍ አባ
ታቸው ዳግማዊ ዓፄ ዳዊት ሲሆኑ እ
ናታቸው ጽዮን ሞገሳ ትባላለች ። ለ
ትምህርት ሲደርሱ በአባታቸው ቤተ
መንግሥት ውስጥ መምህር ተቀጥ
ሮላቸው ንባብና ዳዊት የቃል ት
ምህርት ተምረው ዲቁና ተቀብለው
ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ ሥርዓ
ተ መንግሥትን አጠናቀው ተማሩ
ከዚያም በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድ
በቅዱስ ሚካኤል መሪነት ሌሊት ተነ
ሥተው ሰው ሳያያቸው በመጀመሪያ
ወሎ ክፍለ ሀገር ላስታ አውራጃ ግዳን
ወረዳ ወለቃ ከሚባል ልዩ ቦታ ደርሰው
በቅድስና ከታወቁት ከአባ ዘካርያስ ዘን
ድ የምንኩስናን ደንብና የቅዱሳት መጻ
ሕፍትን ትርጓሜ ተማሩ ከዚያም ቀጥለ
ው ወደ ትግራይ ክፍለ ሀገር ደብረ ዳሞ
ገዳምና አክሱም ጽዮን በመሄድ ከቅዱ
ሳን አበው በመባረክ በትግራይ ክፍ
ላተ ሀገር የሚገኙትን ገዳማት እየዞሩ
በመጐብኘትና በመጸለይ ሥጋቸውን
ስለ ክርስቶስ ፍቅር አድክመዋል ። ከዚ
ያም ወደ ዋልድባ ገዳም ሔደው ከቅዱ
ሳን አባቶች ተባርከው ሲያበቁ ወደ ሰ
ሜን ተራራ ሔደው በቅዱስ ያሬድ የጸ
ሎት ቦታ ሱባዔ በመግባት በጾምና በጸ
ሎት ተወስነው ፵ ቀናት እንደቆዩ
ቅዱስ ያሬድ እመቤታችን ቅድስት ድ
ንግል ማርያምን ያመሰገነበትን እንቅ
ጸ ብርሃን ከድንጋይ ላይ ተቀርጹ አግኝ
ተው ግዕዙን ወደ አማርኛ በደንብ ተር
ጉመው ጽፈው ለብዙ ገዳማት ሰጥተዋ
ል ። ይባላል ። ከዚያ ፫ ጊዜ ወደ ኢየሩ
ሳሌም በእግራቸው በመሔድ ከክርስቶ
ስ መቃብር ሰግደው ጸልየው እንደተመ
ለሱ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም መጥተው
የምንኩስና ማዕርግ ከአባ ተወልደ መ
ድኅን ዘንድ ተቀበሉ ቅስናና ቁምስና
ደግሞ ከአባ ሚካኤል ዘንድ ተቀብለው
እንደገና ወደ ላስታ ተመልሰው እያስተ
ማሩ ዲያቆናትና ቀሳውስትንም ሹመዋ
ል ። ከዚያም በረዶና ብርድ ወደ ሚጸና
በት ዛሬ በስማቸው አቡነ ዮሴፍ ተራራ
ወደሚባለው ወጥተው በዚያ አንባ ላይ
ተቀምጠው ብዙ መነኮሳትንና መናን
ያንን አሰባስበው የክርስትናን እምነት
ና የምንኩስናን ሥርዓት የቅዱሳት መ
ጻሕፍትን ትርጓሜ በደንብ አስተምረ
ው የአንድነት ገዳምን አቋቋሙ ይህን
ም አንባ ደብረ ታቦር ገዳም ብለው ሰየ
ሙት ከዚያም ገነት ብለው ከጥግ ቦታ
ላይ ውሃ በጸሎታቸው ኃይል አፍልቀ
ው ሁለት አብያተ መቅደሶች አሠርተ
ው የእግዚአብሔር አብንና የእመቤታ
ችን የማርያምን ታቦታት አስገብተዋ
ል። እነዚህም ታሪካውያን ቦታዎች የ
ሚገኙት ከቅዱስ ላሊበላ ደብርና ከቅዱ
ስ ይምርሃ ከመሪ ወንዝና ከደብረ ዘመ
ዶ ማርያም ገዳም መካከል ነው ።

ይህ ቦታ ቆላ ሲሆን ደብረ ታቦር የተ
ባለው የአቡነ ዮሴፍ ዓንባ ደግሞ ጭጡ
ያለ ፍጹም ደጋ ነው በዚህም ደብረ ታቦ
ር ብለው በሰየሙት አንባ የሚበቅለው
አዝመራ ገብስ ብቻ ነው ። ከአትክልት
ነጭ ሽንኩርትና ድንች ጐመን ይበቅላ
ሉ ጓሳ ወይም ጭማ የሚባል ሣር ቅርሸ
ባና ጥድ አስታ የሚባሉ ዛፎች ይበቅላሉ
ዕጹር አራዊት በብዛት የሚገኙ ዝንጀሮ
ች ናቸው ሌላው በመጠኑ ነው ። የውሃ
ችግር የለም በዚህ ሁናቴ በሚገኘው ቅ
ዱስ ቦታ የጥቁሬ ዝንጀሮ ብዛት በየገዳ



www.ethiopianorthodox.org

ሙ የሚኖሩትን የመነኮሳቱን አዝመራና በአካባቢው የሚኖረውን የሕዝብ አዝመራ ለመብላት እየመጣ ግራ ስለሚያጋባ የጠባቂ ያለህ ያሰኝ ነበር ። ከጧት እስከ ማታ ድረስ የአዝመራው ጠባቂ ከሌለው ዝንጀሮው አዝመራውን በአንድ ቀን ባዶ መሬት ያደርገው ነበር በዚሁ ደብር ውስጥ ኗሪ የሆነ ሰው የቤተሰብ ብዛት ከሌለው ከዝንጀሮው ብዛት የተነሣ አንድም አዝመራ አይተርፈውም ነበር ።

ጀግናና ጉበዝ ከሆነ አንድ ሰው ለአንድ ማሳ መሬት ለጠባቂነት መመደብ አለበት ደካማና ሰነፍ ከሆነ ግን ሁለት ሰዎች ሆነው ዝንጀሮውን እየተከላከሉ ሊውሉ ይችላሉ ለምሳሌ ለአንድ ገበሬ በዚሁ ገዳም ውስጥ አምስት በሰላዎች ቢኖሩት አምስት ጠባቂዎች ያስፈልጉታል ቤተሰብ ጠባቂዎች ከሌሉት ግን አዝመራው ለዝንጀሮ ቀለብ ሆኖ ይቀራል ።

በዚህ ምክንያት የዚህ ገዳም ኗሪ ምዕመናን በጣም ችግረኞቻ ነበሩ አንዱ ገበሬ ከቤተሰቡ ሰው ቢሞት ከዝንጀሮው ኃይል የተነሣ በኃዘኑ ሰሞን ዕረፍት አያገኝም ነበር ምክንያቱም ዝንጀሮው ጠባቂ የሌለውን አዝመራ በአንድ ቀን ከጥቅም ውጭ ስለሚያደርገው ነው ።

ጻድቁ አቡነ ዮሴፍ ይህንና ይህን የመሰለው ጉዳይ ለአካባቢው ኗሪ ሕዝብ ከፍተኛ መሆኑን ተመልክተው ከዛሬ ጀምሮ ከዚህ ቦታ ላይ አዝመራ እንዳትበሉ የሣር ግጦሽና የአዝመራውን ቅድሚያ ፈቅጀላችኋለሁ ።

ምዕመናን ቀድሚያውን እንዲያይለቅምባችሁ አስተምራችዋለሁ ቅድሚያውን የለቀሙባችሁ እንደሁ ከምሩን እንድትበትኑባቸው ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ ። በተረፈ ግን ከገበሬው አዝመራ አንዱንም ቅንጣት እንዳትበሉ በሥልጣነ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ገዝቻችኋለሁ ብለው ዝንጀሮቹን ገዝተዋቸው ከዚህ ዕለት ጀምሮ ዝንጀሮች ሁሉ በዚያ ከሚገኘው አዝመራ በጻድቁ ግዝት ታሥረው የማይበሉ ሆኑ ምዕመናኑም ዝንጀሮቹም አብረው በሰላም ያለጠብ የሚኖሩ ሆነዋል ። ከዚያ ዕለት ጀምር እስከ ዛሬ ድረስ ዝንጀሮች ሁሉ በአዝመራው ዙሪያ በግጦሽ ሣር ይጠቀማሉ ቀድሚያ ይለቅማሉ እንጅ ከአዝመራው አንድም ፍሬ አይነኩም ከሰበካው ውጭ ግን ጻድቁ ስለአልገዘቷቸው የፈለጉትን አዝመራ በመብላት ይገኛሉ ።

በተጨማሪም ጻድቁ አቡነ ዮሴፍ በደብረ ማርያምና እግዚአብሔር አብ አባብ የሰለጠነበት ስለነበር አባቡን ሰውና እንስሳ እንዳይነድፍ ገዝተውት እስከ አሁን እባቡ ሰውና እንስሳ አይናደፍም ጻድቁ አቡነ ዮሴፍም በሀገሬው ሕዝብ ዘንድ በትምህርታቸውና በትሩፋታቸው የተወደዱ አባት ናቸው ።

ጻድቁ አቡነ ዮሴፍ በዚህ አንባ ላይ በጾም በጸሎት ተወስነው ብዙ መንፈሳዊ ሥራ ሠርተዋል ። የታመመ ፈውሰዋል ሙት አንሥተዋል ። አጋንንትን አባረዋል ደብረ ማርያምንና እግዚአብሔር አብን አቅንተው የሴትና የወንድ ገዳም ለይተው ካቋቋሙ በኋላ ከፈጣሪያቸው ክርስቶስ ጋር በጸሎት ተገናኝተው ስማቸውን ጠርቶ በስማቸው የተማፀነውን ዝከራቸውን የሚዘክረውን ለጸሎት በቆሙባት ቦታ የሚጸለየውን ሁሉ አሥራተ ምህረት ቃል ኪዳን ከፈጣሪያቸው ተቀብለዋል ። ከዚያም ብዙ ዘመን ሳይቆዩ በጾምና በጸሎት ተወስነው ሁለት እጃቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው በዚች አንባ ሲጸልዩ ከቆዩ በኋላ በአንድ መቶ ዕድሜአቸው በዓፄ በዕደ ማርያም ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ላይ ግንቦት ፲፱ ቀን አርፈው በእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከዋሻ ውስጥ በክብር ተቀብረዋል በመቃብራቸውም ልዩ ልዩ ተአምራት ተደርገዋል ዛሬም ይደረጋል ።

ለጸሎት ከቆሙባቸው ቦታዎች ሁሉ ጸበል ፈልቆላቸዋል ። ጸበሉም እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ በሽተኞችን ሲፈውስ ይገኛል ጸበላቸውና የመቃብራቸው አፈር ለአንበጣና ለተምች ለአይጥና ለልዩ ልዩ ተባይ መድኃኒት ነው ደብረ ታቦር ብለው የሰየሙት የጸሎት ቦታቸው ዛሬ የቅዱስ ገብርኤል ጸላት ገብቶበት ይቀደስበታል ።

ቦታውም በስማቸው አቡነ ዮሴፍ ተብሎ ይጠራል ። ይህ ሁሉ ታሪክ ከገድላቸው ተጽፎ ይገኛል ይህ አቡነ ዮሴፍ ይጸልዩበት የነበረው አንባ በኢትዮጵያ እንደሚገኙት ተራራዎች ከፍተኛነት ያለው አንባ ነው ። የኢትዮጵያን መሬቶች ማሳየት የሚችል አንባ ነው ይባላል ። ይህን አስደናቂ አንባ ለመጐብኘት የሚፈልግ ሰው የሚሞቅ ልብስ ይዞ ከቅዱስ ላሊበላ ደብር ተነሥቶ በአምስት ሰዓት ይደርሳል ። ዓንባው ለዓይን አስደሳች ሁኖ ሳለ የብርድ ቦታ ስለሆነ በዚያ ውሎ ለማደር አስቸጋሪ ነገር ነው ሆኖም ያለመከራና ያለችግር የታሪክ ሰው ለመሆን አይቻልምና ይህን ታሪካዊ ቦታ መጐብኘት ያስፈልጋል ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የዚህን ታላቅ ጻድቅ የቅድስና ሥራ ተመልክታና አጥንታ ቅዱስ የሚያሰኘውን ስም ሰጥታ ገድላቸውን ጽፋ በየዓመቱ ግንቦት ፲፱ ቀን በዓለ ዕረፍታቸውን በከፍተኛ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች ።

የዜናው አቅራቢ
አባ ገ/መስቀል ተስፋዬ



# ማርያም መግደላዊት

መግደላዊት በይሁዳ አውራጃ መግደሎን በምትባል ቀበሌ ተወልዳ ያደገች ስሟ በቀበሌው ስያሜ የወጣላት ሲሆን ይህች ሴት ባልተስተካከለ መንገድ ትኖር የነበረች አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ማርያም መግደላዊት በመባል ስሟ ተመዝግቦ የምናገኘው እንደሆነች የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍትና ሊቃውንት ይናገራሉ ።

የማርያም መግደላዊት የመጀመሪያ ሕይወቷና ኑሮዋ እንዴት እንደነበር በታሪክ ሲነገር ስንሰማ በጣም አስደናቂና የሚያስገርምም ሆኖ እናገኘዋለን ።

ማርያም መግደላዊት ማን መሆኗን ለማስታወስ ያህል እንሞክር፦ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው ሁሉ በዝሙት አዳሪነት ሥራ ተሰማርታ የምትኖር ነበረች የዝሙት መንገድ የምታካሂደው ኃጢአት መሆኑን እያወቀች እንጂ ባለማወቅ ወይም በችግር ምክንያት ትፈጽመው አልነበረም በዚሁም ተግባር ከፍ ያለ ገንዘብ ሰበሰበችና ከበርቴ ሆነች ይባላል በተጨማሪም እርሷ በነበረችበት ዘመን ይኖሩ የነበሩት መምህራን አታመንዝር ሲል ሙሴ የጻፈውን ሕግ የሻረ ሕይወት የለውም ለኃጢአቱም ሥርየት አይገኝለትም ስለ ኃጢአት ይቅርታ ማግኘቱ ቀርቶ እንዲያውም በድንጋይ ተወግሮ ይሞታል የሚለውን ወደ ቀቢፀ ተስፋ የሚያደርሰውን የእነርሱን ትምህርት በማዳመጥዋ ተስፋ ከመቁረጧ የተነሳ ከመጥፎ ተግባሯ ለመመለስ ምኞት አልነበራትም በእንዲህ ያለው ያልተስተካከለ ኑሮ ተይዛ ስትባክንና ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ ውስጥ ተቀምጣ ሳለ በሥጋ ብቻ ሳይሆን በመንፈስ የታመሙ ሰዎች ሁሉ ወደ ክርስቶስ እየመጡ የሚፈወሱ መሆናቸውን ሰማች ከዚህም የተነሣ ኃጢአቷን የምታስወግድበት መንገድ ተስፋ በማጣት ቆርጣ የነበረችው የመግደላዊቷ ሴት ይህንን መልካም ዜና በመስማቷ ደስ አላት ምነው ለኔም እንደዚሁ ምህረትን በሰጠኝ ብላ በመመኘት ራሷን ታስመረምር ዘንድ ወደ ክርስቶስ ለመሄድ ቁርጥ ሃሳብ አደረገች ወደ እርሱም ቀርባ ይቅርታን ብትጠይቅ ይቅር እንደሚላት ሙሉ እምነት አደረባት ።

ከዚህ በኋላ በ፫፻ ዲናር አንድ ብልቃጥ ሽቱ ገዝታ ወደ ክርስቶስ እንደወሰደች ወንጌላዊው ዮሐንስ ጽፎታል ።

ከፋሲካም በፊት በስድስተኛው ቀን ኢየሱስ ከሙታን ያስነሳው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ ከዚያም ራት አደረጉለት ማርታም ታገለግል ነበር አልዓዛር ግን ከእርሱ ጋር ከተቀመጡት አንዱ ነበር በዚያን ጊዜ ማርያም መግደላዊት ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱን ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባችው በጠጉርዋም እግሩን አበሰችው ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ የተነሣ መላ ። ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለምን ነው? አለ ይህንም የተናገረ ሌባ ስለነበረ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው የወሰደ ስለነበር ነው ። እንጂ ለድሆች አዝኖላቸው አይደለም ኢየሱስም ድሆችስ ሁል ጊዜ ከናንተ ጋር ይኖራሉና እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም አለ የዮሐንስ ወንጌል ም ፲፪ ቁ. ፲፰ ።

እንደተባለውም ሴቲቱ ከህፃንነቷ ጀምራ የሠራችውን ስህተት ሁሉ አንድ ባንድ ዘርዝራ ተናዘዘች ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ እንዳትበድልና ወደ ቀድሞ ተግባሯም እንዳትመለስ መክሮ ኃጢአቷን አስተሰረየላት ። ከእግዚአብሔር አምልኮትና ከህብረተሰቡ አንድነት ለይቷት የነበረውን ኃጢአት አስወገደላት ከሰላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት መካከል አንደኛዋ ሁና እንድትቆጠር ፈቀደላት ሐዋርያትም እየተዘዋወሩ በሚያስተምረበት ጊዜ በዓለም አካባቢ ሁሉ ስለ ሠራችው ደግነት ስሟ እንዲጠራ ተናገረ ።

እርሷም ይህንን ታላቅ ምሕረት ከክርስቶስ በማግኘቷ እየተደሰተች ያላትን ገንዘብ ሁሉ ለችግረኞች ሰጥታ እርሱን እንደ ተከተለች መጽሐፍ ይናገራል ።

አዎን ማርያም መግደላዊት በመጀመሪያ በሴሰኝነት የምትኖር ኃጢአተኛ ነበረች ይሁን እንጂ በመጨረሻ ጥፋቷን በመረዳት ወደ ኢየሱስ ቀርባ እንባዋን አፍሳ ኃጢአቷን በመናዘዝዋ ሕይወቷን አዳነች እንዲያውም ለሌሎች ኃጢአተኞች ንስሐ እንዲገቡ ጥሩ ምሳሌ ሁና ተገኘች ። እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ይህች ልባም ሴት ለጌታ ያቀረበችው መልካም ሽቱን ብቻ ሳይሆን የኃዘን መግለጫ የሆነውን እንባዋንም ጭምር ከእግሩ ሥር በብዛት አፈሰሰች በዚህ ጊዜ እውነተኛ የሆነው እንባዋ ከልብ ካቀረበችው ገጸ በረከት ጋር የእግዚአብሔርም ፀጋ ስለተጨመረበት በኃጢአት ተጋርዶ የነበረው መንፈሳዊ ዓይኗ ተከፈተላትና ክርስቶስን ለማየት በቃች በእርሱ ጥላ ሥር ተጠልላ ለመኖር ቻለች በመጨረሻም በትንሣኤው ጊዜ እሞታለሁ ብላ ሳትፈራ ወደ መቃብሩ ሽቱ ይዛ በመሄድ የመጀመሪያዋ የትንሣኤው የምሥራች ነጋሪ ለመሆን በቃታለች ።

ንስሐ ዘማዊውን እንደ ድንግል ኃጢአተኛውን እንደ ጻድቅ እንደሚያደርግ ከማርያም መግደላዊት እንማራለን መጽሐፉም ራስህን ለካህን አስመርምር ስለሚል እኛም ራሳችንን ለካህን እናስመርምር ማለት ኃጢአታችንን ተናዘን ንስሐ እንግባ የእናብስትን አፍ የዘጋ ፣ ከታማኝ ወዳጆቹ ጋር በእሳት መካከል የተራመደ አምላክ ዛሬም ቢሆን ተከታ



www.ethiopianorthodox.org

# በዝግ ቤት ታያቸው

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋው ፀዋትወ መከራን ተቀብሎ ተገርፎ ተሰቅሎ ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ በመሞት በሐዲስ መቃብር በበፍታ ተገንዞ ከተቀበረ በኋላ በሶስተኛው ቀን በዕለተ ዕሁድ ከሙታን ተለይቶ ሲነሳ ለደቀ መዛሙርቱ በዝግ ቤት ተሰብስበው ሳሉ ከመካከላቸው ተገኝቶ ሰላም ለሁላችሁ ይሁን በማለት ተገለፀላቸው።

የሰው ልጅ በገነት ሰባት ዓመት ሕጉንና ትእዛዙን ጠብቆ ሥነ ሥርዓትን አክብሮ ኖሯል ከሰባት ዓመት በኋላ የማይገባውን አምላክነት ሽቶ የፈጣሪውን ሕግ በማፍረሱ ከፈጣሪው ጋር ተጣላና ከገነት ወጣ በዚህም ጊዜ የመጀመሪያው ሰው አዳም ስለነበር በደሉንና ጥፋቱን በመገንዘብ በኃዘን በልቅሶ በንስሐ ፈጣሪውን ማለደው። እግዚአብሔርም የልቡን ንፅሕና የሰውነቱን ውርደትና ጉስቁልና ተመልክቶ ንስሐውን በመቀበል አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ሥጋው በመቃብር ነፍሱ በሲኦል ወድቆ በእግረ አጋንንት ተጠቅጥቆ እንዲቆይና ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን ከልጅ ልጁ እንበለ ዘርእ በግብረ መንፈስ ቅዱስ በሥጋ ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቆርሶ እንደሚያድነው ቃል ገብቶ አዳም መሬት ነህና ወደ መሬትነትህ ተመለስ ብሎ በፍርድ መልሶ ወደ መሬት ጥሎት ነበር ።

ይህም ዘመን ሲፈጸም አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ከባሕርይ አባቱ ከመንፈስ ቅዱስ ከባሕርይ ሕይወቱ ሳይለይ ከወዲያ ዓለም ወደዚህ ዓለም በመምጣት ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ተወልዶ በጐል ተጣለ በጨርቅ ተጠቀለለ በስምንት ቀን ግዝረተ አብርሃምን ተቀበለና በአርባ ቀን ወደ ቤተ መቅደስ በመግባት ሕገ ኦሪትን ፈጸመ የለኃጢአት በቀር ሁሉን በትህትና እየፈጸመ እንደ ሕፃናት እየታዘዘ በእየጥቂቱ አድጎ ሰላሳ ዓመት ሲሞላው በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ የባሕርይ ልጅነቱን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ አስመስክሮ ገዳመ ቆሮንቶስ በመግባት አርባ ሌሊትና አርባ ቀን በመጾም የኃጢአት መሰረቶችን አፍርሶና ደምስሶ ሶስት ዓመት ሙሉ በኢየሩሳሌም ዙሪያ በመዘዋወር ወንጌልን አስተማረ በመጨረሻው ጊዜ ለአዳም ንስሐውን ሲቀበል በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ለመፈጸም በአማፅያን ዕድ ተይዞ ለፍርድ በጲላጦስ አደባባይ ቀረበ ።

ከሳሾቹ ጠላቶቹ ሊቃነ ካህናት የሕገ ኦሪት አዋቂዎች ነን የሚሉ ሲሆኑ ተይዞ ለፍርድ እንዲቀርብ ያደረጉበት ወንጀል ሙት አስነሳ ድውይ ፈወሰ ወዘተ. የሚል ነበርና በዚህም ክስ ጲላጦስ ተባባሪ በመሆን ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ጊዜ እንደአስገረፈው ይተረካል ከግርፋቱም በኋላ ካልሞተና ካልተቀበረ በስተቀር የሰው ልጅ የማይድን ስለሆነ የግፍ ግፍ እንዲሰቀል ተደረገ ።

በተሰቀለም ጊዜ የሰው ልጅ በክህደት በድንቁርና ጨለማ ተውጦ አምላክነቱን በመርሳት ግፍ ሲያደርስበት በመስቀል ላይ እንዳለ የአምላክነቱን ድንቅ ሥራ ለመግለጥ ፀሐይ ጨለመ ጨረቃ ደም ሆነ ከዋክብትም እንደቅጠል ረገፉ ምድር ተነዋወጠች መቃብራትም ተከፈቱ ከሞቱትም ሰዎች ብዙዎቹ በሕይወተ ሥጋ ተነስተው ወደ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ሂደዋል ።

አምላክም በለበሰው ሥጋ ለአዳምና ለልጅ ልጆቹ ለእኛ ሲል ባደረገው ቸርነት መከራን ተቀብሎ እንደተሰቀለ በመስቀል ላይ ሳለ በመስኮት ሕያው ሆኖ ወደ ሲኦል በመውረድ አዳምን ከእነ ልጅ ልጆቹ ወደ ገነት መልሶ አግብቶአቸዋል ።

ልክ በ፱ ሰዓትም በፈቃዱ ነፍሱን ከሥጋው ስለለየ ፈጽሞ በሥጋ ሞተ ሞቱንም የተረዳ ዮሴፍ ዘአረማትያስ ከሰባ ሁለቱ አርድእት አንዱ የሆነውና የአይሁድ አለቃ ኒቆዲሞስ ከመስቀል ላይ ሥጋውን በማውረድ በሽቱ አረብርበው በብፍታ ገንዘው ከሐዲስ መቃብር ዐርብ ከ፲፪ ሰዓት ላይ ቀበሩትና በሶስተኛው ቀን ቅዳሜ ለዕሁድ ሌሊት ከሙታን ተለይቶ መቃብር ከፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል በሥልጣኑ ሞትን በሞቱ ሽሮ ተነስቷል ።

ከሙታን መነሳቱንም በመጀመሪያ የአየችና የመሰከረች ማርያም መግደላዊት ናት እርሷም ዓይታ ከመቃብሩ ስለ አጣችው ለደቀ መዛሙርቱ ነገረቻቸው ከነርሱም ጴጥሮስና ዮሐንስ እየሮጡ ሂደው ቢያዩ አጡትና እነርሱም ተመልሰው ከሙታን ተለይቶ መነሳቱን ለጓደኞቻቸው አወሩ ከሌሎችም ጓደኞቻቸው ቀለዮጳና ሌላው ደቀ መዝሙር ሂደው አጥተውት ሲመለሱና

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል

ዮቹን ከጉዳት ለማዳን ዝግጁ ነው ዛሬም እንደነ ማርያም መግደላዊት ንስሐ ገብተው በጸሎት እርዳታ የሚጠይቁትን በምህረት መድረክ ላይ ቁሞ ሙሉ ምህረትን ያደርግላቸዋል በእግዚአብሔር ለሚያምኑና ሰላምን ለሚሹ ሁሉ ሰላሙን ይሰጣቸዋል ።

ማርያም መግደላዊት በእምነት ወደ ጌታ በመቅረቧ የሕይወት መንገድ እንዳገኘች ሁሉ እኛም እንደርሷ ክርስቶስን በሙሉ እምነት ብንከተለው የሥጋዊውም ሆነ የመንፈሳዊ ሕይወታችን እንዲስተካከል ያደርገዋል ልባችንን ከፍተን በእምነት ብንለምነው የሚያረካና የሚያስደስት የዘላለም ሕይወት ይሰጠናል ይሁንና የንስሐ መግቢያ ጊዜው ነገ ሳይሆን ዛሬ ነውና ዛሬውኑ ንስሐ እንግባ ።

ብርሃን ተድላ





# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ሰባት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቍ. 110754
የመልእክት ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org